## በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች

# የልዩ ፍላጎት ትምህርት ዳሰሳ እና ድጋፍ አሰጣጥ መመሪያ




ፌደራል ትምህርት ሚኒስቴር
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
2009

FORMIN.FINLAND.FI
MINISTRY FOR FOREIGN AFFAIRS OF FINLAND

# ምስጋና

ይህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ የተዘጋጀው በዶ/ር ይርጋሸዋ በቀለ ሲሆን ዶ/ር Jan Siska በአማካሪነት እና በእርማት ስራ ተሳትፈዋል፡፡

በተጨማሪ አቶ መሐመድ አቡበከር፤ ሰለሞን ግዛቸው፤ደገፋ አብዲ፤አእምሮ ታደሰ፤ዓሊ ሳኒ፤አለማየሁ ወ/ ቂርቆስ፤ ታምራት ወ/ገብርኤል፤መሰረት በቀለ፤ቡልቶሳ ሒርቆ፤ቦንሳ ቶላ፤ዓለማየሁ ተ/ማርያም፤ብርሃኑ ደንደና፤አላኔ ዋቅጅራ እና ሙሉአለም መኮንን ገንቢ ሀሳብ በማቅረብ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫው ተግባር በተሳካ ሁኔታ እንዲጠናቀቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል

ገፅ ውበት በካሌብ በለጠ

የመምህራን ትምህርት እና የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መስጫ ማዕከላትን አቅም ለመገንባት በኢትዮጵያ እና ፊንላንድ የጋራ ትብብር ፕሮጀክት (2013-2017) ድጋፍ የተዘጋጀ

# ማውጫ


መግቢያ ..... 7

የትምህርት ፍላጎት ዳሰሳ እና የድጋፍ መግለጫ ..... 7

የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው አስፈላጊነት ..... 8

የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው የተዘጋጀበት ዓላማ ..... 9

የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው የአጠቃቀም ዘዴ ..... 9

በክፍል ውስጥ ልዩ ፍላጎትን መለየት ..... 13

የት/ት ቤት ቅድመ ዝግጅት ..... 17

የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው ጥቅም ..... 18

የዳሰሳ እና ድጋፍ አቅጣጫ መግለጫ ..... 21

የማንበብ ተግዳሮት መዳሰስ ..... 21

የማንበብ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ..... 22

የንባብ ዳሰሳ በፊደላት እና ድምፆቻቸው የአንድ ለአንድ ትስስር በሌለባቸው ቋንቋዎች ..... 23

የንባብ ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ ማድረግ ..... 24

የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ዳሰሳ ..... 25

የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ ማድረግ ..... 27

የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት ዳሰሳ ..... 29

የሒሳብ ስሌት ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ..... 30

የመስማት ተግዳሮት ዳሰሳ ..... 32

የመስማት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት ..... 34

መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት ..... 34

ከፊል የመስማት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት ..... 35

የእይታ ተግዳሮት ዳሰሳ ..... 36

የእይታ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት........ 38

የማየት መሳን ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት........ 38

ከፊል የእይታ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት........ 38

የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ዳሰሳ........39

ዝቅተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት ........ 41

ከፍተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት........ 42

በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት ዳሰሳ........ 43

በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት........45

የባህሪ ተግዳሮት ዳሰሳ ........ 48

ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ዳሰሳ........ 50

ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸውን መርዳት........51

የእንቅስቃሴ ተግዳሮት ላለባቸው አካባቢን ምቹ ማድረግ...... ........52

ተደራራቢ ችግር ያለባቸውን መለየት እና ማገዝ........ 53

# የሰንጠረዥ ማውጫ

ሰንጠረዥ 1 ተማሪዎችን ለመለየት እና ድጋፍ ለመስጠት የመምህራን መነሻ ጥያቄዎች ............... 14

ሰንጠረዥ 2 የልዩ ፍላጎት መኖርን ጠቋሚ ምልክቶች........................................................... 19

ሰንጠረዥ 3 የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት መገለጫዎች ........................ ............................................ 26

ሰንጠረዥ 4 የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት መገለጫዎች................................................................ 29

ሰንጠረዥ 5 የመስማት ተግዳሮት መገለጫዎች... .................................................................. 33

ሰንጠረዥ 6 የእይታ ተግዳሮት መገለጫዎች .................................................................... 36

ሰንጠረዥ 7 የአእምሮ ዕድገት ውስንነት መገለጫዎች........................ ........................................ 40

ሰንጠረዥ 8 የመግባባት ተግዳሮት መገለጫዎች ....................................................................... 44

ሰንጠረዥ 9 የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች...................................................................... 48

ሰንጠረዥ 10 የልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ መገለጫዎች ........................................................ 51

# 1. መግቢያ

## 1.1. የትምህርት ፍላጎት ዳሰሳ እና የድጋፍ መግለጫ

በሃገራችን በከፍተኛ ቁጥር የሚገመቱ ልዩ የመማር ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ፍላጎታቸው ሳይታወቅላቸው እና የመለየት እና ድጋፍ የመስጠት ስራ በትምህርት ቤቶች ሳይሰጣቸው ቆይቷል፡፡ በዚህም ምክንያት ከመማር ማስተማሩ ተግባራት ተጠቃሚነታቸው ውስን ከመሆኑም በላይ አዘውትረው ለክፍል መድገምና ትምህርት ለማቋረጥ የተጋለጡ ናቸው፡፡ ልዩ ፍላጎትን መለያና እና ድጋፍ መስጫ የትምህርት መሳሪያ ባለመኖሩ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት መምህራኖች ካለመታወቃቸውም በላይ ተማሪዎቻቸውን መለየትና ድጋፍ መስጠት አልቻሉም፡፡

በመሰረቱ ውጤታማ የሆነ መማር ማስተማር የሚኖረው ተማሪዎች ንቁ ተሳታፊ ሲሆኑ ከመሆኑም በላይ የተማሪዎች ንቁ ተሳትፎ የትምህርት ፍላጎታቸውን ለመለየት እና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችሉ መገለጫዎችን ለማግኘት መልካም አጋጣሚ ይፈጥራል፡፡ ተማሪዎች በትምህርት አቀባበላቸው እና በመማር ፍላጎታቸው የሚለያዩ ሲሆን እንደችሎታቸውና ፍላጎታቸው ለማስተናገድ የሚያስችል የማስተማሪያ ዘዴን መጠቀም የትምህርት ውጤታቸው እንዲሻሻል አስተዋፅኦ ያደርጋል፡፡

በመማር ማስተማሩ ሂደት ላይ የተማሪዎችን ፍላጎት መለየትና ድጋፍ መስጠትን መነሻ ማድረግ የትምህርት ጥራት ማስጠበቂያ ዋነኛ አቅጣጫ ከመሆኑም በላይ ተማሪዎች ከሚጠበቀው በታች የሆነ ውጤት እንዳያስመዘግቡ ይከላከላል፡፡ ድጋፍን ማዕከል ያደረገ የማስተማር ስልትን ውጤታማ ለማድረግ፤መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ንቁ ተመልካች በመሆን የተማሪዎቻቸውን የትምህርት ፍላጎት ዓይነት እና ደረጃ መለየት ይኖርባቸዋል፡፡ መምህራን የተማሪዎቻቸውን የመማር ፍላጎት ፍንጭ ሰጪ ምልክቶችን ከተገነዘቡ እና ከለዩ የድጋፍ አቅጣጫዎችን ለማቀድና ለመተግበር ጥሩ አጋጣሚ ይሆንላቸዋል፡፡ በአጠቃላይ ትምህርታዊ ዳሰሳ እና ድጋፍን መስጠት በመማር ማስተማር ተግባር ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ከመሆኑም በላይ የተማሪዎችን የትምህርት ውጤት እንደሚያሻሽል ይታመንበታል፡፡

የተለያዩ የትምህርት ዳሰሳ ዘዴዎች አሉ ነገር ግን ሁለቱ የዳሰሳ ዓይነቶች በትምህርት ቤቶች የተለመዱ ናቸው። ከእነዚህ የዳሰሳ ዓይነቶች ጥቅል ዳሰሳ (summative assessment) በትምህርት ቤቶች የተለመደ ሲሆን የሚካሄደውም በትምህርት ቤቶች የፈተና ፕሮግራም መሰረት ሲሆን በአብዛኛው በሴሚስተር አጋማሽ ወይም መጨረሻ የሚካሄድ ነው፡፡ ጥቅል ዳሰሳ የተማሪዎችን የትምህርት ግንዛቤ ደረጃ ለመለየት የሚደረግ ምዘና

ሲሆን በየትምህርት ይዘቱ መጨረሻ የሚካሄድ ባለመሆኑ የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመለየት እና በወቅቱ እገዛ ለማድረግ ዕድል አይሰጥም፡፡

በሌላ በኩል መሰረታዊ /ተከታታይ ዳሰሳ (formative assessment) የትምህርት ቤትን ፈተና የመስጫ ዕቅድ ብቻ ሳይጠብቅ በየትምህርት ይዘቱ መጨረሻ እንደአስፈላጊነቱ የሚደረግ ተከታታይ ምዘና ነው። ተከታታይ ዳሰሳ የተማሪዎች የመማር ሁኔታ ዳሰሳ የሚደረግበት ሲሆን ይህ የዳሰሳ ዓይነት የተማሪዎችን የትምህርት አቀባበል፤የችሎታ ደረጃ እና የፍላጎት ዓይነትን ለመለየት ይረዳል፡፡ ይህ የዳሰሳ ዘዴ በተማሪዎች ተከታታይ ምዘና እና ንቁ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ከመሆኑም በላይ የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን መጠቀም ስለሚያበረታታ ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ለመለየትና እና ወቅታዊ ድጋፍ ለመስጠት ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ ይህ ተከታታይ የዳሰሳ ዘዴ አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦች እና ተግባራት ከቀረቡ በኋላ ተማሪዎች መረዳታቸውን ለማረጋገጥ የሚካሄድ በመሆኑ መምህራን ድጋፍ የሚሹ ወይም በድጋሚ ትኩረት ሊያደርጉበት የሚገባቸውን ተግባሮች ለመለየት ይረዳቸዋል፡፡

በበርካታ የዓለማችን ክፍሎች ትምህርታዊ ዳሰሳ የየዕለታዊ መማር ማስተማሩ ተግባር አካል ሆኖ ይገኛል። ጥናቶች እንደሚያሳስቡት ዳሰሳ እና ድጋፍ ጠቃሚ የትምህርት ሥርዓት አካል እንደመሆኑ መጠን የአካቶ ትምህርት በሚካሄድባቸው ቦታዎች መምህራንን በዕውቀት እና በክህሎት በማብቃት የተማሪዎችን ችሎታ እና ፍላጎት በመለየት እና እገዛ በማድረግ፣ የመማር ተግዳሮቶችን በማስወገድ ምቹ የመማሪያ አካባቢን ለመፍጠር ያስችላል፡፡ ለመማር ፍላጎቶች ተገቢና ወቅታዊ ምላሽ የሚሰጡ ትምህርት ቤቶች እና መምህራን የትምህርት ጥራት ለማስጠበቅ በሚያስችል ጎዳና ላይ መሆናቸው ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም እንደዚህ ዓይነት ትምህርት ቤቶች ጥራት ያለው የመማር ማስተማር ሂደት እና ውጤታማ የትምህርት ተቋም እንዲኖራቸው የሚተጉ ናቸው፡፡ ውጤታማ የመማር ማስተማር እንቅስቃሴዎች ላይ ትኩረት ሲደረግ መምህራንን ለዚህ ተግባር በሚያስፈልጋቸው ዕውቀት እና ክህሎት ላይ የስራ ላይ ወይም የአጭር ጊዜ ስልጠናዎች ቢሰጣቸው የበለጠ ውጤታማ ያደርጋቸዋል፡፡ በተጨማሪ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ የት/ት መሳሪያዎች አቅርቦት የመምህራንን እና የትምህርት ቤቶችን ውጤታማነት ያሳድጋል፡፡

## 1.2. የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው አስፈላጊነት

ይህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ የተዘጋጀው በትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ሥራ መረጃ አቅርቦት እና ICT ዳይሬክቶሬት፤ ልዩ የትምህርት ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች በተመለከተ በአዘጋጀው ምደባ መሰረት ነው፡፡ መመሪያው የተዘጋጀው በዋናነት የመምህራንን አቅም በመገንባት ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች ችሎታ እና ፍላጎት በመለየት እገዛ ለማድረግ እንዲረዳቸው ነው፡፡ በተጨማሪ ይህንን የዳሰሰ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ በተገቢው በመተግበር የትምህርት አቀራረብን ለማሻሻል እና ጥራትን ለማሳደግ፣የተማሪዎችን በትምህርት ቤት በውጤታማነት የመቆየት ዕድል ለመጨመር፤ የትምህርት ተሳትፎን ለማሻሻል፤ ክፍል መድገም እና ትምህርት ማቋረጥን ለመቀነስ ይቻላል።

## 1.3. የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው የተዘጋጀበት ዓላማ

የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን ዓላማዎች ከግብ እንደሚያደርስ ይታመናል።

1.3.1. በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ልዩ ፍላጎትን በመለየት ተገቢው ድጋፍ እንዲሰጥ ለማስቻል

1.3.2. መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህጻናት ለመለየት፣ ዳሰሳ ለማካሄድ እና ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችላቸውን ክህሎት በማሳደግ የመተግበሪያ ዘዴዎችን እንዲረዱ እና እንዲተገብሩ ለማድረግ

1.3.3. የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያውን በተግባር ላይ በማዋል ክፍል የሚደግሙ እና ትምህርት የሚያቋርጡ ተማሪዎች ቁጥር ለመቀነስ

1.3.4. መምህራን የማቀድ እና የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን ለመጠቀም የሚያስችላቸውን ብቃት ለማሳደግ

1.3.5. በትምህርት ቤቶች የልዩ ፍላጎት አገልግሎትን በተገቢው በመስጠት እና አስፈላጊ ግብአቶችን በሟሟላት የትምህርት አቅርቦት እና ጥራት ለማሻሻል

**የመምህርነት ሙያዬ የተማሪዎቼን ፍላጎት እንዳውቅ እና እንዳግዛቸው ያስገድደኛል**

## 1.4. የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው የአጠቃቀም ዘዴ

ይህ መመሪያ አስራ አንድ ዋና ዋና የልዩ ፍላጎት ዓይነቶችን፤ ሃያ ሁለት ዝርዝር የልዩ ፍላጎት ዓይነቶችን እና ጠቋሚ ምልክቶችን ያካተተ ሲሆን መምህራን እንዴት መጠቀም እንደሚችሉ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡ አስራ አንዱ ዋና ዋና ክፍሎች መምህራን በቀላሉ በመማር ማስተማር ወቅት ሊለዩአቸው የሚችሉ የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች እና ጠቋሚ (indicators) ምልክቶችን የያዙ ሲሆን ሃያ ሁለቱ ዝርዝር የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች በዋና ዋናዎቹ የልዩ ፍላጎቶች መነሻነት ጥልቅ መገለጫዎችን ያካተቱ ናቸው፡፡ ለምሳሌ ከአስራ አንዱ ዋና ዋና የልዩ ፍላጎት ክፍሎች የንባብ ተግዳሮትን ብንወስድ፤ ፊደልን መለየት ፤ቃላትን ማንበብ እና ዓረፍተነገር ወይም ምንባብን አንብቦ መረዳት ላይ ያሉ ተግዳሮቶችን የዳሰሳ ዘዴዎችን እና የድጋፍ አቅጣጫዎችን ያስቀምጣል፡፡ ለዳሰሳ እና ድጋፍ ለመስጫ በአንድ የልዩ ፍላጎት ላይ የተካተተው በይዘትም ሆነ በቅደም ተከተሉ ለሌሎች የልዩ ፍላጎቶች ከምናደርገው ዳሰሳ እና ድጋፍ ጋር ተመሳሳይነት ስለሌለው እያንዳንዱን ልዩ ፍላጎት በተቀመጠው አቅጣጫ እና በተቀመጠለት ዓላማ መሰረት መተግበር ውጤታማ ያደርጋል፡፡

ከአንድ በላይ የልዩ ፍላጎት ያላቸው ህፃናት ሲያጋጥሙ የፍላጎታቸውን ዓይነት በዚህ መሳሪያ በመለየት ለድጋፍ የተቀመጡ አቅጣጫዎችን እና ይዘቶችን መተግበር ይገባል፡፡ መምህራን የበለጠ ጫና ያሳድራል ቅድሚያ ድጋፍ መጀመር ያስፈልጋል በሚሉት የልዩ ፍላጎት ድጋፍ መጀመር ይችላሉ፡፡ ሌላው አማራጭ ለሁለቱም

ፍላጎቶች ጎን ለጎን ድጋፍ መስጠት ነው፡፡ ለምሳሌ የቋንቋ መምህራን መፃፍ እና ማንበብ ለሚያዳግታቸው ተማሪዎች በሁለቱም ክህሎቶች ላይ ድጋፍ ማድረግ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የተማሪዎቹ የማንበብ ተግዳሮት ትምህርታቸውን የበለጠ ጎድቶታል ብለው ከገመቱ እንደተጨባጭ ሁኔታው የንባብ ክህሎት ድጋፍ ቅድሚያ ሰጥቶ ቀጣዩን ድጋፍ በመጻፍ ክህሎት ላይ ማድረግ ይቻላል፡፡

ይህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ በማንኛውም የአንደኛ ደረጃ (1-8) ክፍሎች ውስጥ መተግበር የሚያስችል ሲሆን ለየክፍሉ የተዘጋጁት የስርዓተ ትምህርት ይዘቶች እና የተማሪዎች የመማሪያ መፅሐፍትን መሰረት በማድረግ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው ባስቀመጠው ቅደም ተከተል በመጠቀም በስራ ላይ ማዋል ጠቃሚ ነው፡፡ በየክፍል ደረጃው ተማሪዎች የልዩ ፍላጎት እንዳላቸው ጠቋሚ ከሆኑ ነገሮች አንዱ ለክፍል ደረጃው የተዘጋጁትን በመፃሐፍት ላይ ያሉ ይዘቶች የመረዳት ወይም የመተግበር ተግዳሮት ማሳየታቸው ነው፡፡ ስለዚህ በክፍል ደረጃው ያሉ ይዘቶችን መነሻ በማድረግ መምህራን የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያውን እንዲተገበሩ ይጠበቃል፡፡

ሰንጠረዥ ቁጥር 2 አስራ አንድ ዋና ዋና የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች እና መገለጫዎች አካቷል፡፡ በሰንጠረዡ የተቀመጡት ይዘቶች ለእያንዳንዱ የልዩ ፍላጎት ዓይነት መገለጫዎችን እንዲሁም መምህራን እነዚህን መግለጫዎች በተማሪዎች ላይ መታየታቸውን ወይም አለመታየታቸውን ምልክት የሚያደርጉበት ቦታ አካተዋል፡፡ መምህራን በአንድ የልዩ ፍላጎት መገለጫዎች ላይ ተማሪዎች መገለጫዎቹን አሳይተዋል የሚሉ ከሆነ ከዚሁ ልዩ ፍላጎት ጋር የተያያዘ ዝርዝር የዳሰሳ ሂደት እና የድጋፍ አቅጣጫ ወደተቀመጠበት ክፍል በመዝለቅ መተግበር ያስፈልጋል፡፡

ለምሳሌ፤ መምህራን በሰንጠረዥ 2 በተቀመጠው መገለጫ መሰረት ህፃናቱ የማንበብ ችግር ገጥሞአቸዋል ብለው ከወሰኑ ወደ ቀጣዩ የማንበበብ ተግዳሮቶች የመዳሰሻ ዘዴዎች እና የድጋፍ አቅጣጫዎች በዝርዝር ወደ ቀረቡበት የመመሪያው ክፍል ማየት እና መተግበር ይጠበቃሉ፡፡ በአጠቃላይ ዳሰሳ እና የድጋፍ አቅጣጫን ለመወሰን መነሻ የሚሆነው መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ በክፍል ውስጥ ተማሪዎች የሚያሳዩዋቸውን ወይም የሚሰሩአቸውን ለየት ያሉ ነገሮች እንደቅድመ ዳሰሳ ጠቋሚ የልዩ ፍላጎት ምልክት አድርገው በመውሰድ ነው፡፡ ለምሳሌ፡- ለክፍሉ ደረጃ የማይመጥን የማንበብ፤ የመፃፍ ወይም የመረዳት ተግዳሮት ሲታይ መምህራን የደሰሳ ተግባር ይጀምራሉ፡፡

የልዩ ፍላጎት ባለሙያ መምህራን ባሉበት ትምህርት ቤት የመደበኛ ክፍል መምህራን ይህንን የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ ከልዩ ፍላጎት መምህራን ጋር በመመካከር ሊተገብሩ ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ የልዩ ፍላጎት ደረጃው ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ መምህራን በሙያተኛ ከታገዙ ልዩ ፍላጎትን በትክክል በመለየት እና ድጋፍ በመስጠት የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪ መምህራን በዳሰሳ ጊዜ ወላጆችን እንደ ተጨማሪ የመረጃ ምንጭ መጠቀም ይገባቸዋል፡፡ ወላጆችን የድጋፍ አቅጣጫው አካል ማድረግ ለውጡን ለማፋጠን እና ድጋፉን በትምህርት ቤት እና በቤት ውስጥ ተከታታይ ለማድረግ ይረዳል፡፡ ይሁንና የዚህ መመሪያ አንባቢ እና ተጠቃሚ ትምህርት ቤቶች እና መምህራን ሊረዱ የሚገባው ፤የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው በዋነኛነት የተዘጋጀው በመደበኛ ክፍሎች ውስጥ ለሚያስተማሩ መምህራኖች ሲሆን በተጨማሪ

በመምህራን ማስልጠኛ ኮሌጆች ፤ በልዩ ፍላጎት ትምህርት ቤቶች እና ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች የትምህርት አገልግሎት በሚሰጡ ተቋማት ውስጥ መጠቀም ይቻላል፡፡ ይህን የትምህርት ድጋፍ መስጫ መመሪያ መጠቀም የሚፈልጉ መምህራን በቅድሚያ በመግቢያው የተቀመጡትን መልዕክቶች እና ከዚህ ቀጥሎ የሚገኘውን የአጠቃቀም ዘዴ ማንበብ ይገባቸዋል፡፡

ለቀላል አጠቃቀም እና በመተግበር ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ስህተቶችን ለማስወገድ ቀጥሎ የተዘረዘሩትን በቅደም ተከተል ቢተገበሩ እጅግ ጠቃሚ ነው ፡፡ የተከበራችሁ መምህራን፡-

- በመግቢያው የሰፈሩትን የትምህርታዊ ዳሰሳ ሐሳቦች፤ቀጥሎም ህፃናትን በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር ጊዜ ለመለየት የሚያስችሉ መገለጫዎችን የካተተውን (Identification) ክፍል እና የዳሰሳ እና ድጋፍ መሳሪያው አጠቃቀም መመሪያ ያንብቡ፡፡
- ሰንጠረዥ 2 አስራ አንዱን ዋና ዋና መገለጫዎች የያዘ ነው ፡፡ በሰንጠረዡ የተካተቱት በሙሉ በቀጣዩ የመመሪያው ክፍል እያንዳንዳቸው በዝርዝር ዳሰሳዎችን እና የድጋፍ አቅጣጫዎችን ይዘው ተካትተዋል። ይህን አስቀድመው ከተረዱ መመሪያውን በተገቢው መጠቀም ይችላሉ፡፡

## የክፍል ጓደኞችን እገዛ ማመቻቸት ከማስተማሪያ ስልቶች አንዱ ነው

### ማስታወሻ

የተከበራችሁ መምህራን ህፃናት የየራሳቸው ተሰጥኦ እና ችሎታ አላቸው በመሆኑም የተማሪዎችን ችሎታ እና ጠንካራ ጎን መፈተሽ፤ ማበረታታት እንዲሁም ለተለየው የልዩ ፍላጎት እገዛ መስጠት የሙያ ግዴታ ሆኖ መወሰድ ይኖርበታል፡፡ ስለዚህ የመማር ተግዳሮቶችን ብቻ ሳይሆን ጠንካራ ጎኖች እና ብቃቶች ጎልተው ሲወጡ ማበረታታት አስፈላጊ ነው፡፡

አንዳንድ ህፃናት በግል ደረጃ ወይም በነፍስ ወከፍ ት/ት ታቅዶ ሊተገበርላቸው ይገባል፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ለክፍል የተዘጋጀውን የስርዓት ት/ት ይዘት በጣም ይቀድማሉ ወይም ወደ ኋላ ይቀራሉ ብለው ካመኑ በአንድ ተማሪ ደረጃ ለሚታቀድ የት/ት ዕቅድ ይረዳ ዘንድ ከዚህ መመሪያ በስተመጨረሻ የተያያዘውን (የነፍስ ወከፍ ድጋፍ መስጫ ቅፅ) መጠቀም ይችላሉ፡፡

ወላጆችን እንደአንድ ግብአት በመጠቀም ስለተማሪዎቹ ተጨማሪ መረጃ ማግኘት ይቻላል። በተጨማሪ በዳሰሳ ጊዜ ምልከታ፤ ቃለ መጠይቅ፣ በመግባባት መረጃ መሰብሰብ፣ ተማሪዎች የሚተገብሩትን በመገምገም እና ሌሎችንም ዘዴዎች መጠቀም ስለተማሪዎቹ የልዩ ፍላጎት ዓይነትና ደረጃ መለየት አስፈላጊ ነው፡፡

ቀጥሎ በቅደም ተከተል (ከ1- 12) በተዘረዘሩት መሰረት ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎችን ለመለየት ይቻላል

1. በክፍል ውስጥ በሚያስተምሩበት ጊዜ ተማሪዎች የሚያሳዩትን ለየት ያለ የመማር ሁኔታ በጥንቃቄ መለየት
2. ልዩ የመማር ፍላጎቶች መገለጫዎች የሚመስልዎትን በማስታወሻ ላይ መመዝገብ
3. በክፍል ውስጥ ያዩአቸውንና የመዘገቡአቸውን የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች በሰንጠረዥ 2 ከተዘረዘሩት አስራ አንዱ ዋና ዋና የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች እና ተያያዥ መገለጫዎች ጋር በማስተያየት ከየትኛው ጋር እንደሚመሳሰሉ መለየት
4. በሰንጠረዥ 2 ከተዘረዘሩት ውስጥ ከየትኛ ጋር እንደሚመሳሰል ከለዩ በኋላ ከሰንጠረዥ 3-10 ካሉት ዝርዝር የደሰሳ እና የድጋፍ አቅጣጫ ውስጥ ከተማሪው ፍላጎት ጋር ተመሳሳይ የሆነውን በመለየት በጥልቀት የተዘረዘሩትን የዳሰሳ እና የድጋፍ ትንተናዎች እና ቅደም ተከተሎች ይመልከቱ፡፡
5. በመረጡት ሰንጠረዥ ውስጥ ንዑስ ዝርዝር የልዩ ፍላጎት አይነቶች ተካተዋል በዚህ መስረት የተማሪው የት/ት ተግዳሮት ከየትኛ ጋር በቀጥታ እንደሚመሳሰል ይለዩ፡፡ ለምሳሌ፡- ፊደል አለመለየት፤ ቃላት አለማንበብ፤ አንብቦ ነገር ግን ይዘትን አለመረዳት ሊሆን ይችላል፡፡
6. ልዩ ችሎታና ተሰጥኦ ያላቸው ልጆች ብዙ ጊዜ ከስርዓተ ትምህርቱ ይዘት በችሎታ ቀድመው ሲገኙ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ተደርገው አይታሰቡም በመሆኑም ከክፍል ደረጃው ስርዓተ ት/ት ይዘት በግላቸው ያለድጋፍ እጅግ ቀደመው የሚገኙ ካሉ መለየትና በተቀመጠው የድጋፍ አቅጣጫ ማገዝ እጅግ ጠቃሚ ነው፡፡
7. በተቀመጠው የዳሰሳ አቅጣጫ በመጠቀም ዝርዝር የመማር ተግዳሮቶቹን በመለየት ድጋፍ ያደርጉ፡፡

## ማስታወሻ

በዳሰሳ ወቅት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም የግኝቱን ትክክለኛነት ያጠናክራል። ስለዚህ የሌሎች መምህራንን፤ የራስዎን ምልከታ፣ ተማሪዎች የሰሯቸውን ወይም የፃፏቸውን፤ በቃል የገለፁበትን መንገድ፤ ወላጆች የተመለከቱትን እና ስጋታቸውን፤ የጓደኛ መግለጫ የመሳሰሉትን መጠቀም የዳሰሳ ውጤቱን ትክክለኛነት ያጠናክራል፡፡

8. በመቀጠል በተገኘው የዳሰሳ ውጤት መሰረት የተቀመጠውን የድጋፍ አቅጣጫ መተግበር አስፈላጊ ነው፡፡
9. ድጋፍ እየተሰጠ ለውጥ መምጣት አለመምጣቱን እና ምክንያቶችን መለየት እና የድጋፍ ማሻሻያ ማድረግ ጠቃሚ ተግባር ነው፡፡
10. ልዩ ድጋፍ እንዲያገኙ የተመረጡት ተማሪዎች በጥሩ ሁኔታ አሻሽለው ሲገኙ ወደ ቀጣዩ የክህሎት ድጋፍ ማምራት ያስፈልጋል (ለምሳሌ ፊደል የማይችሉ ህፃናት በልዩ ድጋፍ

ፊደላትን መለየታቸው ከተረጋገጠ ቃላትን ማንበብ እንዲለማመዱ እገዛ ማድረግ ቀጣዩ ተግባር ይሆናል)፡፡

11. ወላጆች ድርሻቸውን በመውሰድ በቤት ውስጥ ተጨማሪ ድጋፍ እንዲያደርጉ መምህራን ሊያወያዩአቸው ይገባል፡፡
12. በነፍስ ወከፍ ድጋፍ ማድረግ ሲያስፈልግ ከዚህ መመሪያ በስተመጨረሻ ያለውን በአንድ ተማሪ ደረጃ የሚታቀደውን (የነፍስ ወከፍ ድጋፍ መስጫ ቅፅ) መጠቀም ይቻላል፡፡

### ማስታወሻ

ተማሪዎች ልዩ ተሰጥኦ ወይም ችሎታ ስለሚኖራቸው (ለምሳሌ የስዕል፣ የድምፅ፣ አካል እንቅስቃሴ … የማስታወስ ችሎታ፤ ግጥም፣ ዘፈን ወ.ዘ.ተ.) እና ሌሎችንም ልዩ ችሎታዎች በመለየት ከልዩ ፍላጎት ድጋፍ አቅጣጫ ጋር በማቀናጀት የት/ት ተግዳሮቶችን መቀነስ ይቻላል፡፡

መምህራን ሙያቸው አዳዲስ ነገሮችን ለመፍጠር ያነሳሳቸዋል፤ ብቃትም አላቸው በመሆኑም ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ህፃናት በትምህርታቸው ድጋፍ ለማድረግ የራሳቸውን ፈጠራ ይጠቀማሉ ፤አዳዲስ ሀሳቦችን በማፍለቅ አዳዲስ ውጤታማ የማስተማር ዘዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡ ስለዚህ የተከበራችሁ መምህራን የራሳችሁን ፈጠራ እና አዳዲስ ሐሳቦች በመማር ማስተማሩ ላይ በማከል እና በማጠናከር የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ የበኩላችሁን አበርክቱ፡፡

የሙያ ስነ- ምግባር በትምህርት ሙያ ውስጥ ትኩረት የሚሰጠው እና የሚተገበር ነው። የተከበራችሁ መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የዳሰሳ ውጤት በሚስጢር ይጠብቁ እንዲሁም ለትምህርት ብቃት ማሻሸያ መረጃነት ብቻ ይጠቀሙበታል፡፡ እናመሰግናን፡፡

## 1.5. በክፍል ውስጥ ልዩ ፍላጎትን መለየት

መምህራን በዕለት ተዕለት የማስተማር ስራቸው ላይ ከተማሪዎች የሚጠብቋቸውን ውጤቶች ያስቀምጣሉ/ ይመዘግባሉ፡፡ ውጤቱም የሚጠበቀው ለክፍል ደረጃው በተዘጋጀው የት/ት ይዘት መሰረት ሲሆን ይህንኑ በዕለታዊ እና በዓመታዊ የት/ት ዕቅዳቸው ያካትታሉ፡፡ የት/ት ይዘቶችን አስተምረው ሲጨርሱ መምህራን ተማሪዎቻቸው ጨብጠውታል የሚሉትን እና ከአስተማሩት ይዘት ጋር የተያያዘ ዕውቀት እና ክህሎት ባሰቡት እና በአቀዱት መሰረት ተከናውኗል ብለው ይገምታሉ፡፡ ይህንኑ ለማረጋገጥ የተለያዩ የምዘና ስልቶችን ተጠቅመው ምዘና ያደርጋሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በቃል ወይም በፅሁፍ ጥያቄ፣ ሙከራ፣ የክፍል ወይም የቤት ስራ፣ በምልከታ እና በመሳሰሉት፡፡ በውጤቱም አንዳንድ ልጆች በክፍሉ ከተዘጋጀው ይዘት እና ከሚጠበቀው ክህሎት በጣም ዝቅ ብለው ወይም ከፍ ብለው ሊገኙ ይችላሉ፡፡ ውጤታቸውም መምህሩ ከሚያቅዱት እና ከሚጠብቁት ውጪ ሆኖ ሊገኝ ይችላል፡፡ የምዘና ውጤቶች የሚያሳዩት ተማሪዎች ከነበረው የመማር ማስተማር ሂደት ውስን በሆነ መልኩ ተጠቃሚ መሆናቸውን ነው፡፡ የአንዳንድ ተማሪዎች ውጤትም ለመምህራን ያልተጠበቁ ይሆኑባቸዋል፡፡

# መምህር እንደመሆኔ መጠን የተማሪዎቼን ችሎታ እና ፍላጎት እለያለሁ

መምህራን ተማሪዎች ከትምህርት ጋር በተያያዘ የሚያሳዩዋቸው ለየት ያሉ ባህሪያት ወይም መምህራን የማይጠብቋቸው ድርጊቶች ሲከሰቱ በጥንቃቄ እና በአትኩረት መመልከትና ማጥናት ይገባቸዋል፡፡ በተለይ የተማሪዎችን ውጤት በሚመዘኑ ወቅት የአንዳንድ ተማሪዎች ውጤት ያልጠበቁት ሲሆን “ምን” እና “እንዴት” የሚሉትን ጥያቄዎች ማንሳት ተገቢ ነው፡፡ ምን ተከሰተ የሚለው ጥያቄ የተማሪውን የትምህርት ፍላጎት አንድንለይ ይረዳናል፡፡ ይህንንም የመማር ፍላጎት ለመለየት ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የሚያሳዩዋቸውን ወይም የሚያደርጓቸውን ለየት ያሉ ድርጊቶች በማስታወሻ ዘርዝሮ መያዝ፤ የመማር ፍላጎቶችን በጥልቀት በመዳሰስ ለተማሪዎቹ ድጋፍ መስጫ አቅጣጫን ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ ለየት የሚሉ ባህሪያት በዝቅተኛ የትምህርት አቀባበል፤ ከክፍሉ ተማሪዎች ልቆ መገኘት ወይም ልዩ የመማሪያ እና ማስተማሪያ ዘዴ መፈለግ ሊሆን ይችላል፡፡ እንዴት በማለት በመምህራን ሊነሱ በሚችሉ ጥየቄዎች ላይ ድጋፍ የሚሰጥበትን ሂደት ማየት ተገቢ ነው፡፡ ምን ተፈጠረ? እንዴት ድጋፍ እናድርግ? የሚሉት የመምህራን ጥያቄዎች የሚነሱት የተማሪዎችን የት/ት ውጤት በሚመዘኑበት ግዜ በሚያጋጥማቸው ያልተጠበቀ ውጤት ሲሆን ተማሪዎቹ በመማር ማስተማር ሂደት ተጠቃሚ እንዳልነበሩም ጠቋሚ ናቸው።

ቀጥሎ በሰንጠረዥ ቁጥር 1 ውስጥ የተዘረዘሩት ነጥቦች መምህራን በተማሪዎች ውጤት ምዘና ግዜ ሊያነሱት የሚችሉትን ጥያቄዎች እና ምን ሊያግዙ እንደሚችሉ እንዲያስቡና እንዲተገብሩ መነሻ ናቸው፡፡

**ሰንጠረዥ 1 ተማሪዎችን ለመለየት እና ድጋፍ ለመስጠት የመምህራን መነሻ ጥያቄዎች**

| የመማር ተግዳሮቶችን መለየት | ልዩ ችሎታዎችንና ክህሎቶችን መለየት |
|---|---|
| ምን ዓይነት የመማር ባህሪያት ትኩረቴን ሳቡት? | ምን ዓይነት ልዩ ችሎታና ክህሎቶች ትኩረቴን ሳቡት? |
| የመማር ችግሩን በክፍል ውስጥ የተለየ ሚያደርገው ምንድነው? | ልዩ ተሰጥኦና ችሎታውን በክፍል ውስጥ ልዩ የሚያደርገው ምንድነው? |
| ጥልቅ ዳሰሳ በማድረግ የበለጠ ማወቅ ይገባኛል? | ጥልቅ ዳሰሳ በማድረግ የበለጠ ማወቅ ይገባኛል? |
| ለውጥ እንዲመጣ እንዴት ማገዝ ይገባኛል፤ መቼ? | ልዩ ችሎታና ብቃትን የበለጠ ለማበረታታት እንዴት ላግዝ? |

መምህራን ልዩ ፍላጎት ያላቸውን ተማሪዎች የመማር ተግዳሮት እንዲሁም ዝቅተኛ የመረዳት እና ክህሎትን የመጨበጥ አቅም ለመለየት የሚያስችል ጥሩ አጋጣሚ አላቸው፡፡ ይኸውም በየዕለቱ በክፍል ውስጥ በመማር ማስተማር እና በተማሪዎች ተግባር ምዘና ወቅት ነው፡፡

ለምሳሌ፤

- የቋንቋ መምህራን በሚያስተምሩበት ወቅት ፊደል የመለየት ችግር፤ ቃላት የማንበብ ችግር እንዲሁም አንብቦ መረዳት የሚያስቸግራቸውን ተማሪዎች መለየት ይችላሉ፡፡ እንዲሁም መምህራን የተለየ እና ፈጣን በሆን መንገድ ቋንቋ የማዳበር ችሎታ ያላቸውን ተማሪዎችም ለማወቅ ዕድል አላቸው። በተጨማሪ የቋንቋ መምህራን የእጅ ፅሁፍ ችግር የሚታይባቸውን ልጆች መለየት የሚያስችሉ ምልክቶች በክፍል ውስጥ ይመለከታሉ። ለምሳሌ፡- ፊደል ገልብጦ መፃፍ፣ ፊደሎችን በተገቢው ቅርፃቸው አለመፃፍ፣ ቃላትን በትክክል አለመፃፍ እና በአጠቃላይ ለአንባቢ ግልፅ ያልሆነ የእጅ ፅሁፍ ያላቸውን ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሊለዩአቸው ይችላሉ፡፡
- የሒሳብ መምህራንም እንዲሁ የቁጥር ፅንሰ ሐሳብን፣ የሂሳብ ስሌትን፣ የቁጥር ቅደም ተከተልን፣ በንባብ የሚቀርቡ ፅንሰ ሐሳቦችን ከሒሳብ ስሌት ጋር ማዛመድን ፤ የሒሳብ ስሌት ምልክቶችን እና ትርጉማቸውን፤ የሒሳብ ስሌቶችንና ቅደም ተከተሎችን የመረዳት እና የመጠቀም ተግዳሮት የሚያጋጥማቸውን ተማሪዎች መለየት ይችላሉ፡፡ መምህራን በሚያስተምሩበት ጊዜ በጥያቄ እና መልስ፤ በክፍል እና የቤት ስራ ውጤታቸው፤ በቡድን ስራ ተማሪዎቹን ስለሚያዩ የዚህ ዓይነቱ መረጃ ለቀጣይ ዳሰሳ እና ድጋፍ ለመዘጋጀት ይረዳል፡፡
- የማየት ችግር የሚያጋጥማቸውን ተማሪዎች መምህራን አስተውለው መለየት ይጠበቅባቸዋል። ለዚህም ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ የሚያሳዩትን ምልክት መረዳት ያስፈልጋል፡፡ ዓይነስውራን ተማሪዎችን ባላቸው በቀላሉ የሚለይ የዕይታ ችግር መለየት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል መለስተኛ የእይታ ችግር የሚያጋጥማቸውን ተማሪዎች መለየት ቀላል አይሆንም፡፡ ምክንየቱም ተማሪዎቹ በመማር እና በዕለት ከዕለት እንቅስቃሴያቸው እይታቸውን ስለሚጠቀሙ የእይታ ችግር እንዳጋጠመቸው በቀላሉ ማወቅ ያስቸግራል፡፡ የማየት ችግር እንዳለባቸው ለመረዳት በክፍል ውስጥ ያላቸው እንቅስቃሴ ላይ ተገቢ ምልከታ ማድረግ ይጠይቃል፡፡ ዝቅተኛ ወይም መለስተኛ የዕይታ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች የተለያዩ ምልክቶችን ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፡- በጥቁር ሰሌዳ ላይ የተፃፈ ፅሁፍን አይታየኝም ማለት፤ ተነስተው ወደ ጥቁር ሰሌዳው ተጠግተው የተፃፈውን መገልበጥ፤ ደብተር ላይ ያሉ መስመሮችን በትክክል አለመጠቀም እና በገፆች የቦታ አጠቃቀም ላይ አዘውትረው ስህተት መስራት፡፡
- የመስማት ችግር ያለባቸውም ተማሪዎች እንዲሁ ተመሳሳይ የመማር ችግር ያጋጥማቸዋል፡፡ በተለይ አንዳንድ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በት/ት ቤቱ የምልክት ቋንቋ አስተማሪ ወይም አስተርጓሚ ከሌለ ከት/ት ቤት እንዳያስወጧቸው በመስጋት መስማት የማይችሉ መሆኑ እንዳይታወቅ ምንም ምልክት ሳያሳዩ ት/ት ቤት በማየት ብቻ እየተማሩ ይውላሉ፡፡ በሌላ በኩል አብዛኞቹ መስማት የተሳናቸው የማይሰሙ በመሆኑ በቀላሉ ይለያሉ ለዚህም በምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በመታገዝ ይማራሉ ፡፡ ከፊል የመስማት ችግር ወይም መስማት የሚያንገራግራቸው ተማሪዎች ግን የሚሰሙ ስለሚመስሉ እና

በንግግር ቋንቋ ስለሚግባቡ ብዙ ግዜ እነዚህ ተማሪዎች የመስማት ችግር እንዳለባቸው በመምህራንም ይሁን በጓደኞቻቸው አይታወቁም፡፡ ስለዚህ መምህራን ከፊል የመስማት ችግር ምልክቶችን መለየት እና ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ፡- ከሚያሳዩአቸው ምልክቶች ጥቂቶቹ ንግግሮች እንዲደገምላቸው መጠየቅ፣ መምህራን ጥያቄ ሲጠይቋቸው ይደገምልን ማለት፣ የተሻለ የሚሰማውን ጆሮአቸውን ድምፅ ወደሚመጣበት አቅጣጫ ማጋደል፣ ፅንሰ ሀሳቦችን በትክክል አለመረዳት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

- የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸውም ተማሪዎችን መምህራን መለየት ይችላሉ፡፡ በተለይ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ደረጃው ከፍተኛ ሲሆን ተማሪዎቹ በአካላቸው ዕድገት ላይ ምልክቶች ስለሚያሳዩ መምህራን በቀላሉ ይለዩዋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል ዝቅተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ተማሪዎች ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙ ሲሆን በአካላቸው ላይ ምንም ምልክቶች ስለማይታዩባቸው እንደማናቸውም  ተማሪዎች በመደበኛ ክፍል ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ነገር ግን የአእምሮ ዕድገት ውስንነት እንዳለባቸው አይለዩም ድጋፍም አያገኙም፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በአብዛኛው የት/ት ዓይነት ውጤታቸው ዝቅተኛ ይሆናል፤ የመረዳት አቅማቸው ዝቅተኛ ነው፤ ክፍል ይደግማሉ ወይም ት/ት ያቋርጣሉ፡፡

- ሌላው የመማር ተግዳሮት ተማሪዎች የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በተገቢው አለማሳደግና በቋንቋው ተጠቅመው መግባባት አለመቻል ነው፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በተገቢው ደረጃ የአእምሮ ብቃት ቢኖራቸውም ቋንቋቸውን ማሳደግ ግን ይቸገራሉ፡፡  ለምሳሌ፡- የንግግር ፍሰት ችግር፣ የንግግር ድምፆችን በትክክል አለማውጣት፤ የሌሎችን ሐሳብ አለመረዳት ይገኙባቸዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በአካላቸው ላይ ምንም ፍንጭ ሰጪ ምልክቶች ስለማይታዩባቸው ድጋፍ አያገኙም በክፍል ውስጥም ንቁ ተሳትፊ አይሆኑም፡፡

- ይህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ የተዘጋጀው በመደበኛ/regular ክፍል ውስጥ መምህራን እንዲጠቀሙባቸው እና ተማሪዎችን በመለየት ድጋፍ እንዲያደረጉላቸው ነው፡፡ ተማሪዎች የራሳቸው ልዩ ፍላጎት ስላላቸው በዚሁ መሰረት ይህ የዳሰሳ መመሪያ በርካታ የልዩ ፍላጎት ዓይነቶችን፤የመለያ ዘዴዎች እና የድጋፍ አቅጣጫዎችን ይዟል፡፡ ነገር ግን በአንዳንድ ተማሪዎች ላይ በከፍተኛ ደረጃ/sever የሚገመት ልዩ ፍላጎት በክፍል ውስጥ ሲያጋጥም የማጠናከሪያ ት/ት በድጋፍ መስጫ ክፍል ውስጥ፤ በትንንሽ ቡድን እና በነፍስ ወከፍ ደረጃ ተጨማሪ ድጋፍ መስጠት ይገባል፡፡ በአጠቃላይ መደበኛ ክፍሎች በርካታ ተማሪዎች የሚማሩባቸው ከመሆናቸውም በላይ ልዩ የመማር ፍላጎቶች ያላቸው ተማሪዎች የሚማሩበት ፍጥነት እና መንገድ ሊለያይ ይችላል፡፡ ስለዚህ የመምህራን ግንዛቤ እና ክህሎት ለእነዚህ ዓይነት የመማር ፍላጎቶች ምላሽ ለመስጠት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል፡፡

### ማስታወሻ

የተማሪዎችን የመማር ፍላጎት ለመለየት የተለያዩ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ያስፈልጋል። ለምሳሌ:- ከመምህራን፤ ከምልከታ፤ የተማሪዎችን ስራ በመገምገም፤ ለምሳሌ የፅሁፍ፤ የንግግር፤ የተግባር ውጤቶችን መገምገም፤ ከወላጆች እና ጓደኞች መሰብሰብ ግኝቱን ጠንካራ ያደርገዋል፡፡

አንዳንድ ተማሪዎች ልዩ ችሎታና ተሰጥኦ አላቸው፤ ይህም በት/ት ቤት ውስጥ ጎልቶ ይታያል፡፡ ችሎታቸውን የበለጠ እንዲያወጡ ማበረታታት፤ ዕድል መስጠት ጠቃሚ ነው፡፡ ጥንካሬዎችን በመለየት ለልዩ ፍላጎት ድጋፍ የመስጫ መንገድ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## የትምህርት ቤት አስተዳደር ማለት ለአገልግሎት መስዋዕትነት ማለት ነው

### 1.6. የት/ት ቤት ቅድመ ዝግጅት

አካቶ ት/ት ቤት ማለት ሁሉንም ተማሪዎች ያለ አድልኦ እና መገለል ተቀብሎ የሚያስተናግድ ሲሆን በአካል ጉዳታቸው ምክንያት ተማሪዎች መገለል እንዳይደርስባቸው ይከላከላል፡፡ ርዕሰ መምህራንና መምህራን ስለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ቀና አመለካከት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ በተጨማሪ በአካቶ ት/ት ቤቶች ውስጥ ርዕሰ መምህራን ለልዩ ፍላጎት አገልግሎት የሚውሉ ተገቢ ቁሳቁሶች እና የሰለጠነ የልዩ ፍላጎት ትምህርት መምህር ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሐሳቦች በት/ት ቤት ቢተገበሩ ልዩ ፍላጎት ያላቸው ተማሪዎች ተገቢውን የትምህርት አገልግሎት ያገኛሉ፡፡

- ቀና አመለካከትን ማዳበር
- የት/ት ቤቱን ማህበረሰብ ግንዛቤ በማሳደግ መገለልን ማስወገድ
- ምቹ የት/ት አስተዳደር መዘርጋት
- በትምህርት ቤት ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል ማድረግ
- በታቀደ እና በበጀት በተካተተ መንገድ መስራት
- የልዩ ፍላጎት መምህርን ለት/ት ቤቱ መቅጠር/መመደብ

- የድጋፍ መስጫ ማዕከል መክፈትና በተገቢ የመማሪያ መሳሪያዎች ማደራጀት
- በአካቶ ት/ት ላይ ለመምህራን የአጭር ጊዜ የስራ ላይ ስልጠና መስጠት
- ከወላጆች ጋር መስራት የሚያስችል ዕቅድ መንደፍ
- እያንዳንዱ ተማሪ እንደሚማር እና ውጤታማ እንደሚሆን/እንደምትሆን ማመን
- መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያዩአቸውን ክስተቶች በጥንቃቄ ማስተዋል እና መመዝገብ
- ለልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በራሳቸው ተነሳሽነት ድጋፍ ለሚያደርጉ መምህራን ማበረታቻ መስጠት
- ለእያንዳንዱ ተማሪ የት/ት መግለጫ ማህደር ለሚያዘጋጁ መምህራን ድጋፍ መስጠት

## የትምህርት ቤት አስተዳደር ማለት ፍትሀዊነት ማለት ነው

### 1.7 የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያው ጥቅም

ይህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ በመደበኛ የመንግስት፤ የግል ወይም ሌሎች አንደኛ ደረጃ ት/ቤቶች መጠቀሚያነት የተዘጋጀ ነው፡፡

መመሪያው መምህራን የተማሪዎቻቸውን ፍላጎት ለይተው ድጋፍ እንዲሰጡ አቅጣጫ ያስቀምጣል። በመሆኑም ይህንን መመሪያ በአግባቡ በሚጠቀሙ ት/ቤቶች ውስጥ በርካታ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡ በተጨማሪ የልዩ ፍላጎት ተማሪዎች በዚህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ መሰረት ከታገዙ ለክፍል ደረጃቸው የሚገባቸውን እውቀት እና ክህሎት በተገቢው ይጨብጣሉ፡፡

በዚህ የዳሰሳ እና ድጋፍ መስጫ መመሪያ አገልግሎት በሚሰጡ ት/ት ቤቶች የትምህርትን ጥራት ለማስጠበቅ እንደ አንድ ዋነኛ መንገድ ያገለግላቸዋል፡፡በተጨማሪም ክፍል የሚደግሙ እና ት/ት አቋርጠው የሚወጡ ተማሪዎችን ቁጥር ለመቀነስ ይረዳል፡፡

በተጨማሪም መመሪያው በመምህራን ማሰልጠኛ ተቋማት መምህራንን ከማሰልጠን ጋር ከተያያዙ ይዘቶች ጋር አጣምሮ መጠቀም ይቻላል፡፡

# መምህር፡- የተማሪዎች ራዕይ እንዲሳካ ያበረታቱ ፤ ተስፋም ይጫሩባቸው

ሰንጠረዥ 2 ልዩ ፍላጎት መኖርን ጠቋሚ ምልክቶች

| ዋና ዋና ክፍሎች | የተግዳሮት መገለጫዎች | ይታያል | አይታይም |
|---|---|---|---|
| ማንበብ | ◆ ፊደልን መለየት መቸገር | | |
| | ◆ ቃላትን ፊደል በፊደል ማንበብ | | |
| | ◆ ቃላትን ማንበብ አለመቻል | | |
| የእጅ ፅሁፍ | ፊደሎችን አስተካክሎ አለመፃፍ | | |
| | ◆ እርሳስ/ እስኪብርቶ በትክክል አለመያዝ | | |
| | ◆ ለማንበብ የሚቸግር የእጅ ፅሁፍ | | |
| የሂሳብ ስሌት | የቁጥር ፅንሰ ሐሳብን አለመረዳት፤ ለምሳሌ ይበልጣል፣ ያንሳል፣ የሂሳብ ስሌት ምልክቶችን እና አገልግሎታቸውን አለመረዳት (+,X,÷,<,>) | | |
| መስማት | ◆ የንግግር ድምፅን ጨርሶ አለመስማት | | |
| | ◆ የንግግር ድምፅ ዝቅ ሲል ለመስማት መቸገር | | |
| እይታ | አካባቢያቸውን አለማየት | | |
| | ነገሮችን ወደ ዓይናቸው በጣም አቅርቦ ማየት | | |
| ማስታወስ | ◆ የተነገራቸውን ወዲያው መርሳት | | |
| | ◆ የተማሩትን የመረዳት ችግር | | |
| | ◆ የቤት ስራን ወይም እንዲሰሩ የተሰጣቸውን መርሳት እና አለመስራት | | |

| ዋና ዋና ክፍሎች | የተግዳሮት መገለጫዎች | ይታያል | አይታይም |
|---|---|---|---|
| መግባባት | ◆ ሀሳባቸውን መናገር አለመቻል (ከዓይን አፍርነት ወይም ከፍርሀት ያልመነጨ) | | |
| | ◆ መስማት ይችላሉ ነገር ግን የንግግር መልዕክትን አይረዱም | | |
| | ◆ የንግግር ድምፅ በትክክል አለማውጣት | | |
| | ◆ የንግግር ድምፅ በትክክል አለማውጣት | | |
| | ◆ የድምፅ ቅላፄ ከእድሜ እና ፆታ ተለምዶ የተለየ መሆን | | |
| ባህሪ | ◆ በክፍል ውስጥ አዘውትሮ መረበሽ፤ የክፍል ተማሪዎችን እና መምህራንን በመማር ማስተማር ጊዜ ማወክ | | |
| | ◆ በማህበራዊ መግባባት ጊዜ ዓይን ለዓይን መተያየት አለመፈለግ | | |
| | ◆ አዘውትረው ብቸኛ መሆን/ ከዓይን አፋርነት ያልመነጨ | | |
| | ◆ ድብርት መታየት | | |
| ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ | ◆ ከክፍል ደረጃቸው እና ከዕድሜ እኩዮቻቸው በዕውቀት ወይም በክህሎት ልቆ መገኘት | | |
| የእንቅስቃሴ ችግር | ◆ ከቦታ ወደ ቦታ እራስን ችሎ ለመንቀሳቀስ አለመቻል | | |
| | ◆ ከቦታ ወደ ቦታ ለመንቀሳቀስ ድጋፍ መስጫ መሳሪያዎችን መጠቀም | | |
| ተደራራቢ የልዩ ፍላጎት | ◆ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት አስር ዋና ዋና የልዩ ፍላጎት ዓይነቶች ተማሪዎች ከአንድ በላይ ዋና ዋና ምልክቶች ሲያሳዩ | | |

# 2. የዳሰሳ እና ድጋፍ አቅጣጫ መግለጫ

## 2.1. የማንበብ ተግዳሮት መዳሰስ

የማንበብን ተግዳሮት ለመዳሰስ መምህራን በሶስት ዋና ዋና የማንበብ ክህሎቶች ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል። እነሱም ፊደልን መለየት፤ ቃላትን ማንበብ እንዲሁም አንብቦ መረዳት ናቸው፡፡ ተማሪዎች ከእነዚህ ክህሎቶች በአንድ ወይም ከአንድ በላይ በሆኑት ላይ የማንበብ ተግዳሮት ሊያሳዩ ይችላሉ፡፡ መምህራን ዳሰሳ በሚያደርጉበት ጊዜ ከፊደል የመለየት ችሎታ ዳሰሳ መጀመር አለባቸው፤ በመቀጠልም የቃላት ንባብ ችሎታ እና አንብቦ የመረዳት ክህሎቶችን መዳሰስ ጠቃሚ ነው፡፡ ከመሰረታዊው የፊደል መለየት ዳሰሳ ጀምሮ ወደ ከፍተኛው አንብቦ የመረዳት ክህሎት መቀጠል የተማሪዎች የንባብ ተግዳሮት የት ላይ እንደሆነ ለመረዳት ይጠቅማል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ቅደም ተከተሎች የንባብን ተግዳሮት ለመዳሰስ ይረዳሉ፡፡

2.1.1. በፊደላትና በስሞቻቸው/በመጠሪያቸው መካከል አንድ ለአንድ የሆነ ትስስር ባለበት ቋንቋዎች ላይ የንባብ ተግዳሮትን መለየት (ለምሳሌ፡- አማርኛ)

1. ከዚህ በፊት በክፍል ውስጥ ከአስተማሯቸው ፊደሎች በዕጣ ይምረጡና በአንድ ገፅ ላይ በተገቢው ይፃፏቸው፡፡ ለምሳሌ (መ ቢ ሰ ተ ሽ ጠ...)
2. ፊደሎቹን ግልፅ በሆነ መልኩ ይፃፏቸው
3. አንዳንድ ቅጂ በተማሪዎቹ ቁጥር በመምህር እጅ የሚቆይ ያዘጋጁ፤ አንድ ቅጂ ደግሞ ለሚያነቡ ተማሪዎች ያዘጋጁ
4. የተማሪዎችን ቅጂ ዳሰሳ ለሚያካሄዱበት ተማሪ በመስጠት ፊደሎችን በየተራ እንዲያነብ/እንድታነብ ይግለፁ
5. ተማሪዎች በሚያነቡበት ጊዜ ለየተማሪዎቹ ባዘጋጁት ቅጂ ወረቀት ላይ ተማሪዎቹ የተሳሳቱትን ወይም ማንበብ ያልቻሉትን ፊደላት ምልክት ያድርጉ
6. ተማሪዎቹ ሁሉንም ፊደላት ሊያነቡ ይችላሉ ወይም አብዛኞቹን ፊደሎች ላያውቋቸው ይችላሉ
7. ተማሪዎች ፊደል የመለየት ችግር በአብዛኞቹ ፊደላት ላይ ካሳዩ የቃላት ችሎታ ዳሰሳ ማድረግ አያስፈልግም፡፡ ይልቁንም ፊደሎችን እንዲለዩ ድጋፍ መጀመር ይጠቅማል፡፡
8. እንደ አማርኛ ባሉ ቋንቋዎች አንዱ ፊደል አንድ ድምፅ/ስም ስለሚወክልና አብዛኞቹ ፊደላት በቃላት ውስጥ ድምፃቸው ስለማይቀያየር ፊደል መለየት ለቃላት ንባብ ከፍተኛ እገዛ ይሰጣል፡፡
9. ፊደሎችን መለየት የቻሉ ተማሪዎች ቃላት ማንበብ መቻል አለመቻላቸውን ለማረጋገጥ ከዚህ ቀደም በክፍል ውስጥ ከተማሩት ቃላት በዕጣ መርጠው በአንድ ገፅ ላይ ይፃፉቸው፡፡ ለምሳሌ (በላ፣ በሰበሰ፣ መሬት...)

10. ተማሪዎች ቃላቶችን በቅደም ተከተል ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ይንገሯቸው

11. ተማሪዎቹ ሲያነቡ የተሳሳቷቸውን ቃላቶች ወይም ያላነበቧቸውን ቃላቶች ለየተማሪዎቹ ባዘጋጁት ቅጂ ላይ ምልክት ያድርጉ

12. ተማሪዎቹ አብዛኞቹን ቃላቶች ማንበብ ካልቻሉ የቃላት ንባብ ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

13. ተማሪዎች ፊደልን መለየት ከቻሉ ቃላትንም ማንበብ ከቻሉ ነገር ግን ከንባብ ጋር የተያያዙ ተግባራትን በትክክል የማይሰሩ ከሆነ አንብቦ የመረዳት ክህሎት ዳሰሳ ያድርጉላቸው፡፡

14. አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዳሰሳ ለማድረግ ከተማሪው መጽሐፍ ላይ አንድ አጠር ያለ ምንባብ ይምረጡ

15. ከምንባቡ ጋር ተያያዥነት ያላቸው አምስት ጥያቄዎች ያዘጋጁ

16. የመምህሩ ቅጂ ሆኖ ነገር ግን ለእያንዳንዱ ተማሪ አንድ አንድ ቅጂ ያዘጋጁ

17. ተማሪዎቹ ምንባቡን ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ያድርጉ

18. አንብበው ሲጨርሱ ያዘጋጁአቸውን ጥያቄዎች ይጠይቋቸው፡፡

19. አብዛኞቹን ጥያቄዎች በትክክል ካልመለሱ አንብበው የመረዳት ችግር እንዳለ ያሳያል

**መምህራን የተማሪዎች ተስፋ ናቸው፡- ተማሪዎችን ይውደዱ፣ ፍቅርም አሳዩአቸው**

## 2.1.1. የማንበብ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት

አንድ ፊደል አንድን ስም ብቻ በሚወክልበት የቋንቋ ባህሪ እና ፊደሎች በቃላት ውስጥ ድምፃቸውን መቀያየር ካላሳዩ፤ በፊደሎችና ስማቸው መካከል የአንድ ለአንድ ትስስር አለ ይባላል፡፡ እንደዚህ ዓይነት ትስስር በሚያሳዩ ቋንቋዎች (ለምሳሌ አማርኛ) ተማሪዎች ፊደሎችን በትክክል እንዲለዩ ማድረግ ቃላትን እንዲያነቡ ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

ቀጥሎ ያሉትን የድጋፍ አቅጣጫዎች ለተማሪዎች የንባብ ማሻሻያ ይጠቀሙባቸው፡፡

1. ተማሪዎች በቅድሚያ የፊደሎች ድምፅ ከሚናገሩት ቋንቋ የተወሰዱ መሆናቸውን ይገልፁላቸው ምሳሌ ይንገሩዋቸው (በ የሚለው ድምፅ የተወሰደው በሬ፣ በርበሬ፣ በር ወ.ዘ.ተ ከሚሉት ቃላት መሆኑን)

2. በመቀጠል ተማሪዎች እያንዳንዱ ፊደል ያለውን ቅርፅ እና ተያያዥ ድምፅ በትክክል እንዲያውቁ ያግዟቸው
3. ፊደላትና ስሞቻቸው መካከል አንድ ለአንድ ትስስር ባለው ቋንቋ ተማሪዎች ፊደልን በትክክል ከለዩ በመቀጠልም ፊደሎችን በፍጥነት እንዲያነቡ ማገዝ ቃላትን ለማንበብ እገዛ ያደርጋል
4. ቃላትን ማስተማር ሲጀምሩ ከዚህ በፊት የተማሯቸው ፊደሎች ሲቀናጁ እና በፍጥነት ሲነበቡ ትርጉም ያላቸው ቃላቶች እንደሚሆኑ ይገልፁላቸው፡፡ ፊደላትን በፍጥነት ማንበብ ቃላትን ፊደል በፊደል ማንበብን ይከላከላል (ምሳሌ መ ን ገ ድ) እነዚህ ፊደላት በአንድ ላይ ሲሆኑና በፍጥነት ሲነበቡ (መንገድ) ተብሎ ትርጉም ያለው ቃል ይሆናሉ በማለት ያስረዷቸው
5. አንዳንድ ተማሪዎች ፊደላትን እና ቃላቶችን በትክክል ማንበብ ችለው ነገር ግን አንብበው መረዳት ይቸግራቸዋል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች የንባብን ፅንሰ ሐሳብ ወይም መልዕክት ደረጃ በደረጃ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከምንባቡ ውስጥ የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር ካነበቡ በኋላ ይዘቱ ላይ ማወያየት፡፡ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ መሰረታዊ መልዕክት የያዙትን ቃላቶች ይለዩና ተማሪዎች መልዕክታቸውን እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ በዚህ ሂደት በምንባቡ ውስጥ የተካተቱትን ዓረፍተ ነገራት እያንዳንዳቸው የያዙትን መልዕክት በቅደም ተከተል ማወያየት በመጨረሻም በምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ላይ ማወያየት
6. ርካርዶችን፤ የስዕል መግለጫዎችን እና ሌሎችንም አጋዥ መረጃዎችን ይጠቀሙ
7. በፍጥነት ማንበብ፤ አንብቦ የመረዳትን ክህሎት ስለሚያሳድግ ተማሪዎች ፊደላትን፣ ቃላትን እና ምንባብን በሚያነቡበት ጊዜ ፍጥነትን እንዲጨምሩ ያግዙአቸው
8. ተማሪዎች ድምፃቸውን ከፍ አድርገው ሲያነቡ በትክክል ማንበባቸውን ካረጋገጡ በኋላ ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ያለማምዷቸው
9. የተማሪዎች የንባብ ችሎታ መሻሻል ቀጣይት እንዲኖረው ክትትል እና ድጋፍ አይለያቸው

## 2.1.2 የንባብ ዳሰሳ በፊደላት እና ድምፆቻቸው የአንድ ለአንድ ትስስር በሌለባቸው ቋንቋዎች

ፊደሎች እና ድምፆቻቸው አንድ ለአንድ ትስስር በሌለባቸው ቋንቋዎች መሰረታዊ የንባብ ክህሎት መነሻው በቋንቋ ውስጥ ያለውን የድምፅ ቅንጅት መረዳት ነው፡፡ ምክንያቱም ፊደላት በተለያዩ ቃላት ውስጥ የተለያዩ ድምፆችን እና ትርጉሞችን ስለሚሰጡ ነው፡፡ ለምሳሌ በቁቤ አፋን ኦሮም አጭር ወይም ረጅም አናባቢዎች በቃላት መጀመሪያ፣ መካከል ወይም መጨረሻ መጠቀም የሚቻል ሲሆን ይህም የተለያዩ ድምፆችን ስለሚወክሉ ነው ለምሳሌ (maal, Nagaa, Mana) 'a' አጭር ወይም ረጅም አናባቢ በመሆን የቃላቱ አነባበብና ትርጉም እንዲቀያየር ታደርጋለች፡፡ በተጨማሪ ረጅም አናባቢ (aa) የሚያሳየው የድምፅ መርዘም ሲሆን ረጅም ተነባቢ (..yy..) የሚያሳየው ድምፅ በጫና እንደሚነበብ ነው፡፡

በአንደነዚህ ዓይነት ቋንቋዎች ተማሪዎች ሲማሩ የማስተማር ዘዴው ማተኮር ያለበት የቋንቋው የድምፅ ሥርዓት በፅሁፍ ምን እንደሚመስል ማስረዳት እና ማሳወቅ ላይ ነው:: ቃላትን ለማንበብ የእነዚህን ድምፆች ቅንጅት መለየት ይገባል ይሁንና አንዳንድ ተማሪዎች ይህንን የድምፅ ቅንጅት እና በቃላት ላይ የሚያመጣውን የትርጉም ለውጥ በተገቢው ላይረዱት ይችላሉ:: ከዚህ በታች የተዘረዘሩ ቅደም ተከተሎች መሰረታዊ የንባብ ተግዳሮቶችን ለመለየት ይረዳሉ::

1. ረጅም እና አጭር ተነባቢ የሆኑ ፊደላቶችን ለይተው ያወጡ ምሳሌ (EE, HO, B, KK, CH,M..)
2. ቅንጅቱ አንድ እና ሁለት አናባቢዎችን ያካተተ ይሁን ለምሳሌ (I, a,e,ii,aa,ee)
3. የመረጧቸውን በአንድ ገጽ ላይ ያዘጋጁዋቸው
4. በመምህር እጅ ላይ የሚያዝ ለእያንዳንዱ ተማሪ አንድ አንድ ቅጂ በማዘጋጀት በሌላው ቅጂ ተማሪዎች ድምፆቹን እንዲጠሩ ያድርጉ
5. ተማሪዎቹ ሲያነቡ የሰሯቸውን ስህተቶች በየተማሪዎቹ ቅጂ ላይ ይመዝግቡ
6. ተማሪዎቹ የድምፅ ቅንጅቱን እና የትርጉም ለውጡን ካልተረዱ ቃላትን አንብቦ መረዳት ያስቸግራቸዋል
7. ይህን ለማረጋገጥ ተማሪዎቹ ከተማሯቸው ቃላት በእጣ መርጠው በአንድ ገፅ ላይ ለንባብ ያዘጋጁአቸው እና ተማሪዎቹ እንዲያነቡ በማድረግ ለእያንዳንዱ ተማሪ ያዘጋጁት ቅጂ ላይ ተማሪዎቹ የተሳሳቱትን ድምፆች ይመዝግቡ
8. ተማሪዎቹን በረጅም እና አጭር አናባቢ እና ተነባቢ ፊደላት የሚኖረውን የአነባበብ ድምፅ ልዩነት ይጠይቋቸው
9. የድምፅ ልዩነቱ በቃላት ላይ የሚያመጡትን የትርጉም ልዩነት ካልተረዱ ድጋፍን ይሻሉ

## ተማሪዎች ራዕያቸው ተስፋ እንዲኖረው እናበረታታቸው

### 2.1.2.1. የንባብ ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ ማድረግ

የድምፆችን ቅንጅት እና የፊደሎችን ጥምረት መለየት መሰረታዊ ነው:: በመቀጠል ቃላትን ለማስተማር ድምፆች እንዴት የቃላትን ትርጉም እንደሚለውጡ ማስተማር ያስፈልጋል

ከዚህ ቀጥሎ ያለውን ቢተገበሩ የተማሪዎችን የንባብ ችሎታ ማሻሻል ይችላሉ::

1. በቅድሚያ እያንዳንዱ ፊደል የሚወክለውን ድምፅ ያስተምሮአቸው
2. በመቀጠል አንድ (አናባቢ ወይም ተነባቢ) ያለውን ድምፅ እና ሁለት (አናባቢ ወይም ተነባቢ) ያለው የድምፅ ልዩነት ያስተምራቸው ምሳሌ (Mo, Moo, Ma)
3. አጭር ወይም ረጅም አናባቢ ወይም ተነባቢ በቃላት ውስጥ ድምፅ እና ትርጉምን እንዴት እንደሚቀይሩ ያስተምሯቸው ምሳሌ ይስጡ
4. በንባቡ ማስተማር ጊዜ አብዛኛው ትኩረት መሰጠት ያለበት በቃላት ንባብ ላይ ነው። ቃላትን ሲያነቡ ትርጉሞቻቸውንም አብረው ይማሩ
5. ተናጠል ድምፆችን ለማስተማር አጠር ያለ ጊዜ በቂ ነው ምክንያቱን ተናጠል ድምፆች ትርጉም ስለሌላቸው ተማሪዎችን ለማገዝ ወደ ቃላት ማስተማር ትኩረት ማድረግ ያስፈልጋል
6. የንባብ ፍጥነትን ማሻሻል አንብቦ የመረዳት ችሎታን ስለሚያሻሽል ተማሪዎች ቃላቶችን በፍጥነት እንዲያነቡ ያግዟቸው፡፡ በሀገራችን የንባብ ፍጥነት ደረጃ በይዘጋጅለትም ጥናቶች እንደሚያሳዩት ስልሳ ቃላት በደቂቃ ማንበብ እንደ መነሻ ችሎታ ተደረጎ ይታያል
7. የተማሪዎችን የንባብ ብቃት ለመለየት እንዲቻል ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲያነቡ ቢደረግም በትክክል ማንበብ ሲችሉ ግን ድምፅ ሳያሰሙ እንዲያነቡ ማለማመድ ይገባል
8. ንባብን ሲያስተምሩ ካርዶችን ፣ የስዕል መግለጫዎችን እንዲሁም ሌሎች አጋዥ ቁሳቁሶችን መጠቀም አይዘንጉ
9. አንብቦ የመረዳት ክህሎትን ለማሻሻል የንባብን ፅንሰ ሐሳብ ወይም መልዕክት ደረጃ በደረጃ መረዳት ይኖርባቸዋል፡፡ ለምሳሌ ከተማሪው መፅሐፍ ላይ አንድ አጭር ምንባብ ይምረጡ፡፡ ከምንባቡ ውስጥ የመጀመሪያውን ዓረፍተ ነገር ካነበቡ በኋላ ይዘቱ ላይ ማወያየት፣በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ መሰረታዊ መልዕክት የያዙትን ቃላት ይለዩና ተማሪዎች መልዕክታቸውን እንዲረዱ ያድርጉ፡፡ በዚህ ሂደት በምንባቡ ውስጥ የተካተቱትን ዓረፍተ ነገራት እና እያንዳንዳቸው የያዙትን መልዕክት በቅደም ተከተል ማወያየት ፣ በመጨረሻም በምንባቡ አጠቃላይ መልዕክት ላይ ማወያየት
10. ክትትል እና ድጋፍ አስፈላጊ ስለሆነ የተማሪዎችን የንባብ መሻሻል ዘላቂነት ያግዙ

## 2.2. የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ዳሰሳ

የእጅ ፅሁፍ ክህሎት እንደ አንድ የተማሪዎች ብቃት መለኪያ ተደርጎ ይቆጠራል ፡፡ጥናቶች እንደሚያሳዩት ለክፍሉ ደረጃ በማይመጥን ሁኔታ ተገቢውን የእጅ ፅሁፍ ክህሎት አለማዳበር በተማሪዎች ውጤት ላይ ጫና ከማድረጉም በላይ የተማሪዎችን በራስ መተማመን እንደሚጎዳ ይገለፃል፡፡ በበርካታ ት/ት ቤቶች ተማሪዎችን የመለየት እና ድጋፍ የመስጠት ስራ በማይሰራበት ሁኔታ ቁጥራቸው በርካታ የሚሆን ተማሪዎች የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት የሚታይባቸው ሲሆን እነዚህ ተማሪዎች ሳይለዩ እና ድጋፍ ሳይደረግላቸው በትምህርት ቤት ይቆያሉ፡፡ መምህራንም እነዚህን ተማሪዎች ደካማ የእጅ ፅሁፍ ያላቸው ብለው ከመግለፅ ያለፈ ድጋፍ እያደረጉላቸውም። መምህራን የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ያለባቸውን ተማሪዎች ለመለየት በክፍል ውስጥ በርካታ

አጋጣሚዎች አሏቸው፡፡ ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 3 ውስጥ ከተካተቱት የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ጠቋሚዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተግዳሮቶች የሚያሳዩ ከሆኑ በእያንዳንዱ መገለጫ ፊት ለፊት አዎ ታይቷል በሚለው ስር ምልክት በማድረግ ችግሩን ይለዩ በመቀጠልም የተዘረዘሩትን የድጋፍ አቅጣጫዎች በመተግበር ለውጥ እንዲመጣ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 3 የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት መገለጫዎች

| የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት መገለጫ | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|
| ◆ እርሳስን በሚፅፉበት ወቅት በተገቢው መያዝ መቸገር | | |
| ◆ በሚፅፉበት ጊዜ በተገቢው አቀማመጥ አለመቀመጥ | | |
| ◆ ብዙ ጊዜ የፃፉትን ማጥፋት | | |
| ◆ የፊደሎችን አቅጣጫ ማዘበራረቅ | | |
| ◆ የፊደሎችን መጠን እና ቅርፅ ማዘበራረቅ | | |
| ◆ የደብተር መስመሮችን በተገቢው አለመጠቀም | | |
| ◆ የደብተር ገፆችን በትክክል አለመጠቀም | | |
| ◆ ተገቢው የፅሁፍ ፍጥነት አለመኖር | | |
| ◆ ፊደላትን ከቃላት ውስጥ ማጓደል | | |
| ◆ የፊደላትን ተቀፅላ ወይም ቅርፅ አለመለየት | | |
| ◆ ሲፅፉ በዓይናቸው ወደ ደብተራቸው በጣም መጠጋት | | |
| ◆ የፅሁፍ ስራን ለመጀመር መፍራት | | |
| ◆ ሲፅፉ ብዙ ስህተት መስራት | | |
| ◆ ሲጽፉ ወዲያው እጄን አመመኝ ወይም ደከመኝ ማለት | | |
| ◆ በፊደሎች እና ቃላቶች መካከል ቦታ አለመመጠን | | |
| ◆ የማይነበብ የእጅ ፅሁፍ | | |
| ◆ ክፍላቸው እየጨመረ ሲሄድ ሐሳባቸውን በፅሁፍ ለመግለፅ መቸገር | | |

### 2.2.1 የእጅ ፅሁፍ ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ ማድረግ

- በቅድሚያ ለተማሪዎች የእርሳስ አያያዝ ናሙና ማሳየት
- ሲፅፉ እንዴት መቀመጥ እንዳለባቸው ማሳየት
- ሲፅፉ የደብተራቸውን ትክክለኛ አቀማመጥ ማሳየት
- በአየር ላይ ሙሉ እጃቸውን በማንቀሳቀስ የፊደላት እና የቁጥሮችን ቅርፅ የሚፅፉ አስመስለው እንዲለማመዱ ማገዝ
- በመቀጠል መዳፋቸውን እና ጣቶቻቸውን ብቻ በማንቀሳቀስ የፊደላት እና የቁጥሮችን ቅርፅ የሚፅፉ አስመስለው እንዲለማመዱ ማገዝ
- በአየር ላይ ሲፅፉ የፊደሎችን ቅርፅ እንዲያስታውሱ ማገዝ፤ በዚህም ለእጅ ፅሁፍ ያላቸው ፍራቻ ይቀንሳል፤ ለመፃፍም ይደፍራሉ
- በቃላቶች እና በፊደላት መካከል ቦታን የመገመት ችሎታን እንዲያዳብሩ ማለማመድ
- መስመራቸው ጎልቶ የተሰራላቸው ደብተሮች በመጠቀም መስመር ይዘው እንዲፅፉ  ማለማመድ
- ለመፃፍ ምቹ ስሜት የሚፈጥሩባቸውን የእርሳስ ወይም የእስክሪፕቶ ዓይነት እንዲመርጡ ዕድል መስጠት
- ፊደሎችን ከመፃፋቸው በፊት ቅርፃቸውን  እንዲመለከቱ ማበረታታት
- የፊደሎችን አቅጣጫ ተመሳሳይ ለማድረግ አጭር መስመሮችን ወደ ተመሳሳይ አቀጣጫ እየፃፉ እንዲለማመዱ ማድረግ፤ ለምሳሌ (IIIIII. . . )
- ተመሳሳይነት የሚበዛባቸውን ፊደላት የሚለዩበትን ነገር ማሳየት ሲጽፉ ማለማመድ
- የእጅ ፅሑፍ ህጎችን ማስተማር ለምሳሌ፡- ከግራ ወደ ቀኝ መፃፍ፤ ገፆችን በተገቢው መጠቀም፤ በገጽ ላይ ከጎን እና ከጎን እንዲሁም ከላይ እና ከታች ክፍት ቦታ መተው፤
- በአንዱ ገጽ ላይ በትክክል ፅፈው ሲጨርሱ ወደ ሚቀጥለው መገልበጥ ወ.ዘ.ተ.
- እያንዳንዱ ፊደል እንዴት እንደሚፃፍ ማስተማር
- ቃላትን መፃፍ ማለማመድ
- የእጅ ፅሁፍ ስራን ከዕለት ተዕለት ተግባር ጋር አያይዘው መፃፍ እንዲለማመዱ ያበረታቱዋቸው። ለምሳሌ፡- ደብዳቤ  መፃፍ፤ ማስታወሻ መፃፍ፣ የቤት ዕቃዎችን መዘርዘር፤ የሚወዷቸውን  የኳስ ተጫዋቾች ስም መፃፍ ወ.ዘ.ተ

- የፊደሎችን መጠን እንዲያመሳስሉ አሁንም አንድ ቁጥር የምትመስል መስመር በመጻፍ ሁሉንም በእኩል መጠን እንዲፅፉ ማለማመድ። ይህን ካደረጉ በኃላ ፊደሎችን ወይም ቃላቶችን በደብተራቸው ላይ በትክክል መጻፍ መጀመራቸውን ይከታተሉ ድጋፍም ያድርጉላቸው
- ለእነዚህ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ የእጅ ፅሑፍ ተግባራት ሲሰጡ ጥቂት ተጨማሪ ጊዜ መስጠት
- የእጅ ፅሑፍ ድጋፍ ሲያደርጉ ሊሻሻል የሚፈልጉትን ክህሎት ዓይነት ተራ በተራ ያለማምዷቸው እንጂ ሁሉንም የፅሑፍ ብቃት ክህሎት በአንድ ጊዜ አይጠብቁ ለምሳሌ፡- አንድ ጊዜ ስለፊደል መጠን፤ ቀጥሎ ስለትክክለኛ ፊደላት ቅርፆች ፤በመቀጠል በፊደላት መካከል ቦታን መመጠን ወ.ዘ.ተ.፡፡ ይህ እያንዳንዱን ክህሎት በተገቢው እንዲጨብጡ ይርዳቸዋል፡፡
- የእጅ ፅሑፋቸውን ስሜት ጎጂ በሆነ አስተያየት አይግለጹላቸው
- ተማሪዎች የራሳቸውን የእጅ ፅሑፍ የሚገመግሙበት መስፈርት ይስጧቸው በመስፈርቱም መሠረት እንዲያሻሽሉ ይንገሯቸው፡፡
- እንዲጽፉ የሚፈለገውን ፅሑፍ መጠን ይመጥኑላቸው በመልሳቸው ውስጥ ዋና ዋና ሀሳቦች መካታታቸውን ከግንዛቤ ያስገቡት
- የእጅ ፅሑፍ ስራ ሲሰጣቸው በትንሽ በትንሹ በየተራ እንዲሰሩ እና እንዲያጠናቅቁ ዕድል ይሰጧቸው፡፡
- የተማሪዎችን ዕውቀት ለመመዘን ከፅሑፍ ስራ ውጪ ያሉ ተግባራትንም ዋጋ ይሰጧቸው፡፡ ለምሳሌ፡- በቃል ሀሳብን የመረዳት ችሎታ፣ በተግባር የሚሰሩ መግለጫዎችን ወ.ዘ.ተ.
- የእጅ ፅሑፍ ማሻሻል ትዕግስት እና ተከታታይ ድጋፍ ስለሚፈልግ መምህር እባክዎ ይህንን ከግምት ውስጥ ያስገቡ
- ክትትል እና ድጋፍ አይለያቸው
- ተማሪዎች ዕድል ካገኙ ማንኛውንም ነገር መስራት ይችላሉ ስለዚህ የመስራት ዕድል እንፍጠርላቸው

## ለተማሪዎች የአባትነት/የእናትነት ፍቅር እንስጣቸው

## 2.3. የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት ዳሰሳ

የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት በዓይነቱም ይሁን በደረጃው ከተማሪ ወደ ተማሪ ይለያያል፡፡ ተማሪዎች ትምህርት በሚጀምሩበት ጊዜ ቁጥሮችን እና ቁጥር ማለት ምን እንደሆነ ፅንሰ ሀሳቡን ላይረዱት ይችላሉ፡፡ አንዳንድ ልጆች ወደ ትምህርት ቤት ሄደው ትምህርት በሚጀምሩበት ጊዜ ቁሶችን በቅርጻቸው፣ በመጠናቸው፣ በቀለማቸው ማደራጀት ያስቸግራቸዋል፤ ቅደም ተከተልንም በትክክል አያዘጋጁም፤ እንዲሁም ቁሳቁሶችን ማነፃፀር (ማወዳደር) ያዳግታቸዋል፡፡ ለምሳሌ (ትንሽ/ትልቅ፣ ረጅም/አጭር፣ ከአጭር ወደ ረጅም መደርደር ወይም በተቃራኒው፤ቁጥሮችን በቅደም ተከተል መጥራት (1 2 3 4 . . .)፤ ቁጥሮችን መለየት እና ማወዳደር ወ.ዘ.ተ.፡፡ ይሁንና መምህራን እነዚህን ምልክቶች በመለየት እና ዳሰሳ በማድረግ ድጋፍ መስጠት ይኖርባቸዋል፡፡

ተማሪዎች እነዚህን ከላይ የተጠቀሱትን እና ቀጥሎ በሰንጠረዥ 4 ውስጥ የተዘረዘሩትን የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት መገለጫዎች ማሳየት ወይም አለማሳየታቸውን ለማወቅ ከቁጥር ጋር የተያያዙ ተግባራትን በመስጠት (እንደክፍላቸው ደረጃ) ከሒሳብ ስሌት ፅንሰ ሐሳብ ጋር የተያያዙ ተግባሮችን ይሰጧቸው፤ የሰሩትንም በመመልከት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት የእጅ ጽሑፍ ተግዳርት መገለጫዎች ጋር ያመሳስሉአቸው፡፡ ተማሪዎች ከተካተቱት ጠቋሚዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተግዳሮቶች የሚያሳዩ ከሆኑ በእያንዳንዱ መገለጫ ፊት ለፊት አዎ ታይቷል በሚለው ስር ምልክት በማድረግ ችግሩን ይለዩ፤ በመቀጠልም የተዘረዘሩትን የድጋፍ አቅጣጫዎች በመተግበር ለውጥ እንዲመጣ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 4 የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት መገለጫዎች

| የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት መገለጫ | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|
| በንግግር ቋንቋ ጥሩ የሚጠቀሙ፤የማንበብ ችግር የማይታይባቸው፤ የእጅ ፅሑፍ ችግር ሳያጋጥማቸው ነገር ግን የቁጥር ፅንሰ ሐሳብን መረዳት የሚቸግራቸው፤ ለምሳሌ ከፍተኛ/ዝቅተኛ፣ ያንሳል/ ይበልጣል ትንሽ/ትልቅ ወ.ዘ.ተ | | |
| ቁሶችን በተጠየቀው ቅደም ተከተል ማስቀመጥ/መደርደር መቸገር | | |
| ቁጥሮችን እና ቁሶችን ወይም ምስሎችን የማዛመድ ተግዳሮት ለምሳሌ (፡፡ እና 4) (.....እና 5) | | |
| - ቁጥሮችን በቅደም ተከተል መጥራት አለመቻል<br>ለምሳሌ (1 2 3 4 - - - ፤ 5 10 15 - - - )<br>(የቁጥር መስመር ላይ መስራት መቸገር) | | |
| 2ኛ ክፍል እና ከዚያ በላይ ሆነው ቁጥሮችን ለማስላት ጣቶቻቸውን አዘወትረው መቁጠር | | |

| የሂሳብ ስሌት ተግዳሮት መገለጫ | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|
| ሒሳባዊ ግምትን ማስላት መቸገር፤ ለምሳሌ (ትንሽ አሸዋ እና የሚበልጥ አሸዋ፣ እሩቅ እና ቅርብ) ፅንሰ ሐሳቡ እንደክፍል ደረጃው ሊለያይ ይችላል፡፡ | | |
| አቅጣጫን በትክክል የመለየት ችግር (ከላይ/ከታች...) | | |
| የተማሩትን የሂሳብ ስሌት መርሳት | | |
| የገንዘብ ምንዛሬን እና መጠንን እንዲሁም የጥቅም መጠናቸውን አለመረዳት | | |
| የሂሳብ ማስያ ምልክቶችን፣ ትርጉማቸውን እና ተግባራቸውን አለመረዳት ለምሳሌ (5+5, 5X5, 2-2, 2+2) | | |
| በእጣ ወይም አጋጣሚ የተደረደሩ ቁጥሮችን ለመጥራት መቸገር ለምሳሌ (6,8,11,22,45) | | |
| ከቁጥር ጋር የተያያዙ ተግባራትን ለመስራት ደስተኛ አለመሆን | | |
| በመደመር ወይም በመቀነስ ጊዜ ሂደቶችን እና የስሌት ፅንሰ ሐሳቦችን አለመረዳት ለምሳሌ (5+5 = 10 or 10-5= – | | |
| ሰዓት፣ ቀን፣ ወራት፣ ወቅት የመሳሰሉትን ሐሳቦች በትክክል አለመለየት | | |
| የቃላት ፕሮብሌም/ስሌትን አንብቦ በመረዳት የማስላት ችግር | | |

## ተማሪዎች ዕድል ከተሰጣቸው ተግባሮችን በትክክል መስራት ይችላሉ

### 2.3.1. የሒሳብ ስሌት ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት

- በዕለት ከዕለት ተግባራት ጋር በማያያዝ የቁጥሮችን ፅንስ ሐሳብ ይግለጹላቸዋል፡፡ ለምሳሌ ሁለት ብርቱካን ከአንድ ብርቱካን እንዴት እንደሚበልጥ፣ ሁለት ሙዝ መብላት አንድ ሙዝ ከመብላት የበለጠ ሆዳችንን እንደሚሞላ /እንደሚያጠግብ ወ.ዘ.ተ
- የቁጥር ቅደም ተከተልን በቃል እንዲጠሩ ማለማመድ፤ ደረጃ በደረጃ መጠኑን ማሳደግ፣ ትናንሽ እንጨቶች በመቁጠር መጠቀም፤ በማጨብጨብ ብዛትን መቁጠር፤ በእግር መሬት በመምታት መቁጠርን ማለማመድ ወ.ዘ.ተ.

- የተማሪዎችን የክፍል ውስጥ አቀማመጥ በቁጥር በመጥራት ቁጥራቸውን እንዲለዩ ማድረግ
- የቤትሥራ በመስጠት ወላጆች ወይም ታላላቅ እህቶችና ወንድሞች ድጋፍ እንዲያረጉላቸው ማበረታታት
- የነጠላ ቁጥሮችን ማስላት እስከሚለዩ ድረስ የአንድ አለኝ፤ ሁለት አለኝ ስሌቶችን ማስተማር ማዘግየት
- ነገሮችን በዓይን በማየት እንዲገምቱ ያለማምዷቸው
- የሒሳብ ስሌት ምልክቶችን ትርጉም እና ተግባር በደንብ ማሳወቅ ይህንንም ደረጃ በደረጃ ማስተማር፤መጀመሪያ መደመር (+)ትርጉሙን እና በቁጥር ስሌት እንዴት እንደምንጠቀምበት ማስረዳት፡፡ ቁሳቁሶችን በመጠቀም መደመር በቁሳቁሶች ቁጥር ላይ የሚያመጣውን ለውጥ ማስረዳት መደመርን በደንብ ሲያውቁ ወደ ቀጣዮቹ (መቀነስ፣ ማባዛት እና ማካፈል - - - በየደረጃው ማስተማር)
- አንደኛ ክፍል ወይም ይህ ድጋፍ ሲሰጥ ተማሪዎች ጣቶቻቸውን ከቆጠሩ ወይም ደብተራቸው ላይ መስመሮችን በመስራት ስሌትን ለማከናወን ከተጠቀሙ አይከልክሏቸው ምክንያቱም የስሌትን ፅንሰ ሐሳብ እንዲረዱ ያግዛቸዋል፤ በቀጣይ ግን ጣቶቻቸውን ሳይቆጥሩ አስበው እንዲሰሩ በቃል እንዲይዙ ያለማምዷቸው
- አዲስ ክህሎትን ማስተማር ሲጀምሩ በመጀመሪያ ከቀላል እና ተጨባጭነት ካላቸው የስሌት ስራዎች ይጀምሩ፤ከዚያም የቁጥሮችን መጠን በመጨመር የማሰብና የመስራት ችሎታቸውን ማበልፀግ
- የሴሌት ስራዎችን ሲያስረዷቸው ግልጽ በሆነ መንገድ ማስረዳት እና እንዲሰሩ ማበረታታት ፍርሐትን ይቀንስላቸዋል፡፡
- በትኩረት የሚሰሩበትን ቦታ/ሁኔታ ማመቻቸት እና በድምፅ የሚረብሻቸውን ነገር ማስወገድ
- ለመጻፊያ የሚያስፈልጉ ነገሮችን ማዘጋጀት
- ከተማሪዎች ጋር በማቀናጀት ድጋፍ እንዲያገኙ ማመቻቸት
- ቀለም ያላቸው እርሳሶችን፣ ከለሮችን በመጠቀም የሂሳብ ስሌት ሂደቶችን ማሳየት
- የቃላት ፕሮብሌምን ለማስረዳት፤ መጀመሪያ በቃል በማንበብ ቁጥር ነክ ሐሳቦችን ማወያየት፣ከቃላት ፕሮብሌሙ ቁጥር ነክ ሐሳቦችን ለይቶ ማውጣት እና ማወያየት፤  አስልተው መልስ እንዲሰጡ ማበረታታት ፤ በመቀጠል የቃላት ፕሮብሌሞችን በማንበብ በሚጠየቀው መሰረት አስልተው መልስ እንዲሰሩ ማድረግ
- ተማሪዎቹ ክትትል እና ድጋፍ አይለያቸው

**የተማሪዎች ራዕይ መታየት የሚጀምረው መምህራን በተማሪዎቻቸው ላይ በሚኖራቸው እምነት ነው (Albert Einstein)**

## 2.4. የመስማት ተግዳሮት ዳሰሳ

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በበርካታ ትምህርት ቤቶች ተገቢውን የዳሰሳ እና የድጋፍ አገልግሎት ሳያገኙ በትምህርት ቤት ይቆያሉ፡፡ በአብዛኛው ትምህርት ቤቶች የምልክት ቋንቋ አስተርጋሚዎች እና የልዩ ፍላጎት መምህራን ባለመኖራቸው መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ ሳይታወቁ እና አስፈላጊውን የማስተማሪያ ዘዴ ሳያገኙ ይቀራሉ፡፡ አንዳንድ ተማሪዎች ውስን የመስማት ችሎታ ሊኖራቸው ይችላል ወይም ምንም ላይሰሙ ስለሚችሉ በቃል/በድምፅ ብቻ ትምህርት በሚቀርብበት ትምህርት ቤት ከሚቀርበው ትምህርት ተማሪዎቹ ተጠቃሚ አይሆኑም፡፡ እነዚህ ተማሪዎች ትምህርት ቤት እንደገቡ የመስማት መጠን ዳሰሳ ቢደረግላቸው እና የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ በክፍል ውስጥ ቢኖራቸው በትምህርታቸው ውጤታማ የሚያደርጋቸው አቅም አላቸው፡፡

ከፊል የመስማት ችግር የሚያጋጥማቸው ተማሪዎች ተግዳሮታቸው ሳይታወቅላቸው በትምህርት ቤት ውስጥ ይቆያሉ፡፡ በቃል መግባባት ስለሚችሉ በከፊል የመስማት ተግዳሮት እንዳለባቸው የክፍል መምህራን ሳያውቁላቸው እና ድጋፍ ሳይሰጡአቸው ይቀራሉ፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በትምህርታቸው ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር በከፊል አለመስማት ስለሚታይባቸው ዳሰሳ እና ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ ድጋፍ የማይደረግላቸው ከሆነ በትምህርታቸው ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ያሳድራል፡፡

ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 5 ውስጥ መስማት መሳን እና ከፊል የመስማት ተግዳሮት መገለጫዎች ተዘርዝረዋል። የመስማት ተግዳሮቱን ለመለየት ከተማሪዎቹ ጋር በቃል ለመግባባት ወይም ለመነጋገር ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ። በዚህም ጊዜ የመስማት መሳን ምልክቶች ሊታዩ ይችላሉ፡፡ በሰንጠረዡ ውስጥ ከተዘረዘሩት መገለጫዎች ጋር የሚመሳሰሉትን ምልክት ያድርጉባቸው፤ በመቀጠል ስለድጋፍ አቅጣጫ የተዘረዘሩትን ይተግብሯቸው፡፡

ሰንጠረዥ 5 የመስማት ተግዳሮት መገለጫዎች

| ዋና ዋና መገለጫዎች | ዝርዝር መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| መስማት መሳን | ከኋላቸው ሆነው ሲጠሩአቸው አለመስማት | | |
| | ሲያናግሯቸው የከንፈር እንቅስቃሴ እና የፊት አገላለጥ ምልክቶችን በመከተል ለመረዳት መሞከር | | |
| | የቃል ንግግርን አለመረዳት/ አለመስማት | | |
| | ሐሳብን ለመሰንዘር የሰውነት ክፍሎችን እንቅስቃሴ በመጠቀም ለመግልፅ መሞከር | | |
| | ከጊዜ በኋላ መስማት የተሳናቸው ከሆኑ ጥራቱ የተጓደለም ቢሆን በቃል መናገር መሞከር ነገር ግን አለመስማት | | |
| | ሲወለዱ ጀምሮ መስማት የተሳናቸው ከሆኑ የንግግር ድምፆችን አለማውጣት | | |
| ከፊል የመስማት ተግዳሮት | በዙሪያቸው ፀጥታ ሲኖር በተሻለ መስማት | | |
| | አዘወትረው የጆሮ ህመም እንዳለባቸው መግለፅ | | |
| | አዘወትረው ለጥያቄዎች አግባብ ያልሆነ መልስ መስጠት | | |
| | በቃል ትዕዛዝ ጊዜ ሌሎች ጓደኞቻቸው የሚሰሩትን በማየት መተግበር | | |
| | ከተለመደው የድምፅ መጠን በጣም ከፍ ወይም በጣም ዝቅ አድርገው መናገር | | |
| | ለቃል ጥያቄ መልስ ለመመለስ መዘግየት | | |
| | አዘወትረው የተባለው እንዲደገምላቸው መጠየቅ | | |
| | የድምጾችን መነሻ ለመለየት በዓይናቸው መፈለግ | | |
| | ጭንቅላታቸውን የተሻለ በሚሰማው ጆሮአቸው አቅጣጫ ማዘንበል (ለመስማት ሲፈልጉ) | | |
| | የድምፅ /ንግግር መነሻ አካባቢ ተጠግተው መቆም ወይም መቀመጥ | | |
| | ተናጋሪው ድምፃቸውን ከፍ እንዲያደርጉ አዘወትረው መጠየቅ | | |
| | ንግግር በሚበዛባቸው ተግባራት የመሳተፍ ፍላጎት መቀነስ | | |
| | ተረቶች/ታሪኮች ሲነበቡ ለማዳመጥ ፍላጎት ማጣት | | |

## 2.4.1 የመስማት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

### 2.4.1.1. መስማት ለተሳናቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት

መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች የምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ ካገኙ በመደበኛ ክፍል ውስጥ ገብተው መማር ይችላሉ፡፡ ይሁንና መደበኛ ክፍል ከመግባታቸው በፊት በቅድመ መደበኛ ክፍሎች የምልክት ቋንቋ ስልጠና ሊሰጣቸው ይገባል፡፡ የምልክት ቋንቋ የሚችሉ የመደበኛ ክፍል መምህራን ባሉበት የሚሰሙ እና የማይሰሙ ተማሪዎች ተቀላቅለው መማር ይችላሉ፡፡ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች በተገቢው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ የምልክት ቋንቋ ስልጠና ማግኘት አለባቸው ፤ይህ ከሆነ በምልክት ቋንቋ አስተርጓሚ አማካኝነት መማር ይችላሉ፡፡ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት መስማት የተሳናቸውን በመደበኛ ክፍል ውስጥ ለማገዝ ይረዳሉ፡፡

- በቅድመ መደበኛ ወይም በዝግጅት ክፍል የምልክት ቋንቋ ክህሎት ስልጠና መስጠት
- መስማት ከተሳናቸው ተማሪዎች ጋር መጫወት፣ ተግባራትን በፊት ለፊት በሚያዩበት ሁኔታ መተግበር፣
- ወደ ክፍል  ሲገቡ ትምህርት ከመጀመርዎ በፊት የሁሉንም ተማሪዎች ትኩረት መሳብ፤ በዚህም ጊዜ መስማት የተሳናቸው ተማሪዎች መምህር መግባቱን እና ትምህርት መጀመሩን ስለሚረዱ በዓይናቸው ይከታተላሉ
- የዕለቱ ትምህርት ስለምን እንደሆነ በቅድሚያ በግልጽ ያስረዱ ስለዚህ ተማሪዎቹ ስለምን ሊማሩ እንደሆነ ይገባቸዋል፡፡
- ሐሳብን ለማስረዳት ተጨማሪ ፍንጭ ሰጪ ነገሮችን ይጠቀሙ፤ ለምሳሌ በፊትዎ ስሜት አገላለጥ፤ በከንፈር እንቅስቃሴ እና ሌሎችም፡፡ ይህ ነገሮችን በተሻለ የመረዳት እድል ይፈጥርላቸዋል፡፡
- መምህራን በክፍል ውስጥ ፊታቸው ወደብርሃን ሆኖ ተማሪዎች በቀላሉ ሊመለከተዋቸው ይገባል። በተጨማሪ የምልክት ቋንቋ ትርጉምን ለመመልከት አስተርጓሚው ወይም መምህሩ እጆቹ ለተማሪዎቹ በደንብ መታየቱን ማረጋገጥ
- ተማሪዎቹ ሊያስረዱአቸው የፈለጉትን ፅንሰ አሳብ ካልተረዱ ተጨማሪ የማብራሪያ ዘዴ ይጠቀሙ ለምሳሌ አጋዥ የስዕል መግለጫ ወ.ዘ.ተ.
- በሚያስተምሩበት ጊዜ ስለቁሳቁሶች ማብራሪያ ሲሰጡ የሚታዩ አጋዥ ነገሮችን በስዕል ወይም በትክክለኛው ቁሳቁስ በመጠቀም ያብራሩላቸው
- በምልክት የተነገራቸውን ሐሳብ በመቀጠል በጽሑፍ ያሳዩአቸው
- የተገለፀላቸውን ነገር ተማሪዎች መልሰው እንዲገልፁ ያድርጓቸው
- ተጨማሪ ድጋፍ (tutorial) ፕሮግራም ያዘጋጁላቸው እና ያልገባቸውን ይድገሙላቸው
- ሲያስተምሩ ተግባሮችን በየተራ ያድርጓቸው ለምሳሌ፡- መናገር፣ መፃፍ፣ በምልክት ቋንቋ መተርጎምን በየተራ ይጠቀሙ ምክንያቱም መስማት የተሳናቸው ሁሉንም ባንዴ መከታተል ስለሚያስቸግራቸው

- ለሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እኩል ዕድል መስጠት
- መስማት የተሳናቸው ለረጅም ሰዓት አስተርጓሚን እና ምልክትን ሲያዩ ዓይናቸው እና አእምሮአቸው ስለሚደክሙ በመካከል ጥቂት ሌላ ተግባራትን ያካትቱ
- ድጋፍ እና ክትትል አይለያቸው

**ጥሩ መምህራን ይገልፃሉ፤ በጣም ጥሩ ምመህራን ሰርተው ያሳያሉ፤ እጅግ በጣም ጥሩ መምህራን አእምሮን ያነቃቃሉ/ይኮተኩታሉ**

### 2.4.1.2. ከፊል የመስማት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

- በከፊል መስማት የሚያስቸግራቸው ተማሪዎች ጥቂት ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ብቻ በመደበኛ ክፍል ውስጥ ያለችግር ይማራሉ፡፡
- በክፍል ውስጥ ተማሪዎች መምህሩን ሊሰሙ በሚችሉበት ቦታ መቀመጥ እንዲችሉ ይፍቀዱላቸው፡፡
- የተከበሩ መምህር ፡- ድምፅዎን ሁሉም ተማሪዎች መስማት በሚችሉበት መጠን ይናገሩ
- የሚቻል ከሆነ ተማሪዎች ድምፅን አጉልቶ የሚያሰማ መሣሪያ (hearing aid) በጆሮአቸው እንዲያደርጉ ያመቻቹላቸው፤ ይህ ካልሆነ ለወላጆች ምክር በመስጠት የድምፅ ማጉያ መሳሪያ እንዲገዙ መገፋፋት
- በሚጽፉበት ጊዜ ጎን ለጎን የሚያስረዱ ከሆነ በከፊል መስማት የሚቸገሩ ልጆች ከአፍ እንቅስቃሴ የሚረዱትን እንዳያጡ ተራ በተራ ይተግብሯቸው
- በክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቁጥር አነስተኛ ከሆነ በግማሽ ክብ አቀማመጥ ወንበሮቹን በማመቻቸት ሁሉም ተማሪዎች መምህራቸውን እንዲያዩቸው ማድረግ
- በሚያስተምሩበት ጊዜ በክፍል ውስጥ እና አካባቢ የሚረብሹ ድምጾች ካሉ በማስወገድ ተማሪዎች ድምፅዎን በደንብ እንዲሰሙ ምቹ ሁኔታ ይፍጠሩ
- ተማሪዎቹ ለብቻቸው የትምህርት ተግባራትን እንዲሰሩ፣ በቡድን ስራ ተባብረው እንዲሰሩ እና ማህበራዊ መግባባት እንዲያዳብሩ ያበረታቱዋቸው
- ተማሪዎቹ ሲናገሩ በደንብ ያዳምጧቸው፤ እርስዎም ጥያቄ ይጠይቋቸው እና መልስ ለመመለስ እንዲችሉ በቂ ጊዜ ይስጧቸው
- ለሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እኩል ዕድል መስጠት
- ተማሪዎቹ ክትትል እና ድጋፍ  አይለያቸው
- አንድን ክህሎት ሲጨርሱ ወደ ለቀጣዩ ክፍሎት ስልጠና ያዘጋጁአቸው፡፡

## 2.5. የእይታ ተግዳሮት ዳሰሳ

ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በአንድ ወይም በሌላ ሁኔታ የማየት ተግዳሮት ያሳያሉ፤ ይሁንና የተግዳሮቱ ዓይነት እና ደረጃ ከተማሪ ወደ ተማሪ የተለያየ ይሆናል፡፡ ስለዚህ መምህራን የእይታ ተግዳሮት መገለጫዎችን በመለየት ድጋፍ ለማድረግ ይችላሉ፡፡ ከፊል የማየት ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ብዙም የማይታወቁ ይሁን እንጂ የእይታ ተግዳሮቱ የትምህርት ውጤታቸው ላይ ጉዳት ያመጣል፡፡ በሌላ በኩል ማየት የተሳናቸው ተማሪዎች በቀላሉ ስለሚለዩ ጥቂት ትምህርት ቤቶች እነሱን ለማስተማር ዝግጅት ያላቸው ስለሆነ ሲቀበሏቸው አብዛኞቹ ትምህርት ቤቶች ተቀብለው አያስተምሯቸውም፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 6 ያሉት የዕይታ ተግዳሮት መገለጫዎች ተማሪዎቹን ለመለየት እና ለማገዝ ይረዳሉ። ተማሪዎች ከተካተቱት ጠቋሚዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ተግዳሮቶች የሚያሳዩ ከሆኑ በእያንዳንዱ መገለጫ ፊት ለፊት አዎ ታይቷል በሚለው ስር ምልክት በማድረግ ችግሩን ይለዩ፤ በመቀጠልም የተዘረዘሩትን የድጋፍ አቅጣጫዎች በመተግበር ለውጥ እንዲመጣ እገዛ ያድርጉላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 6  የእይታ ተግዳሮት መገለጫዎች

| ዋና ዋና ክፍሎች | የእይታ ተግዳሮት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| ማየት መሳን | ሙሉ በሙሉ ስለማያዩ ከቦታ ወደ ቦታ ለመጓዝ/ መንቀሳቀስ ድጋፍ ይሻሉ | | |
| | አንዳንድ ተማሪዎች ትልልቅ ቁሳቁስ ማየት ይችላሉ ነገር ግን አነስተኛ ነገሮችን ማየት አይችሉም | | |
| | አንዳንዶች የብርሃን አቅጣጫን ወይም ብርሃን ያያሉ ሌሎች ደግሞ ምንም ብርሃን አይታያቸውም | | |
| | ጽሑፍ በትልልቁም ቢጻፍ አይታያቸውም | | |
| | በዕለት ተዕለት ተግባራት በመንካት፣ በማዳመጥ፣ በማሽተት፣ በመቅመስ በመሳሰሉትን አካባቢያቸውን ይለያሉ | | |
| | አንዳንዶች ሲራመዱ በሰውነታቸው ወደ ፊት/ወደኋላ/ ወደጎን ጋደል ይላሉ ወይም ሰውነተ ለንቋሳ መስለው ይታያሉ | | |
| | ደካማ የአካል ቅንጅት ይታይባቸውል፡፡ | | |

| ዋና ዋና ክፍሎች | የእይታ ተግዳሮት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| በክፊል የማየት ተግዳሮት | በመደበኛ መጠን የተፃፉ ጽሑፎችን ማንበብ መቸገር (በእይታ ምክንያት) | | |
| | በሥዕል እና (ማፕ) በአገር ካርታ ላይ ያሉ ትንንሽ መግለጫዎችን እና ስሞችን ለማየት መቸገር | | |
| | በዓይን እና እጅ ቅንጅት ሥራ ላይ ደካማነት መታየት | | |
| | ያልተለመደ እይታ ፤ ዓይንን ማጨናቆር እንዲሁም በተለይ ብርሐን ላይ በሚያዩበት ጊዜ የፊትን ገጽታ ማጨማደድ | | |
| | የእይታ ትኩረት የሚፈልጉ ስራዎች ላይ የምቾት ስሜት ማጣት | | |
| | የርቀት ወይም የቅርብ እይታ ችግር | | |
| | እይታቸው ጉም ወይም ዳመና በመሰለ ነገር ውስጥ መሆን | | |
| | በእጅ ጽሑፉ ላይ የፊደሎችን እና ቁጥሮችን ቅርፅ በተገቢው አለመፃፍ፣ መስመር በትክክል አለመጠቀም፣ ሲፅፉ የተዛባ የቦታ አጠቃቀም ማሳየት | | |
| | የቀለማትን ተመሳሳይነት እና ልዩነትን አለማየት | | |
| | ሲራመዱ ብዙ ጊዜ በእቃዎች ወይም ነገሮች መደናቀፍ ወይም መጋጨት | | |
| | ነገሮችን ለማየት እራሳቸውን ወደ ሚያዩት ነገር ማዘንበል/ማስጠጋት | | |
| | ሲያነቡ ወይም ሲጽፉ መፃፋቸውን ወይም ደብተራቸውን ወደ አይናቸው በጣም ማስጠጋት | | |
| | አንዳንዶች ከጥቁር ሰሌዳ ላይ የተፃፈውን ለመገልበጥ ወደ ጥቁር ሰሌዳው መሄድ | | |
| | አንዳንዶች እንደሚታያቸው ቦታ ወደ ፊትለፊት ወይም ከዋላ ለመቀመጥ መፈለግ/መጠየቅ | | |
| | ከጎን የማየት ችግር (ለምሳሌ፣ በክፍሉ በአንዱ ጠርዝ ሆነው ወደ መሀል ፤ ወደ መምህር ወይም ወደ ጥቁር ሰሌዳው ማየት መቸገር | | |
| | በእይታ ጊዜ አንድ ዓይናቸውን መሸፈን | | |

## 2.5.1. የእይታ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት

### 2.5.1.1. የማየት መሳን ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

- የትምህርት ቤቶችን አካባቢዎች፣ የመማሪያ ክፍሎችን፣ መፀዳጃ ቤቶችን፣ የመጠጥ ውሃ ቧንቧዎች ያሉበትን ቦታ እና በትምህርት ቤት ውስጥ የውስጥ ለውስጥ መንቀሳቀሻ መንገዶችን ምቹ ማድረግ፡፡
- ስለ ትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ እና አገልግሎቶች ስለሚገኙባቸው ቦታዎች መግለጫ መስጠት
- በቅድመ መደበኛ ወይም በዝግጅት ክፍል የብሬል ክህሎት ስልጠና መስጠት
- የብሬል የተማሪው መጽሐፍት በትምህርት ቤት እንዲገኙ ማድረግ
- ወደ ክፍል ሲገቡም ሆነ ሲወጡ የቃላት መግለጫ መስጠት/ሰላምታ ሊሆን ይችላል፣
- ተማሪዎቹ ፊት ለፊት እንዲቀመጡ ዕድል መስጠት
- ሲያስተምሩ ድምፅዎ ለሁሉም ተማሪ የሚሰማ ይሁን
- ለሁሉም ተማሪዎች ተሳትፎ እኩል ዕድል መስጠት
- ከፈቃደኛ ረዳት ተማሪ ጋር አብረው እንዲቀመጡ እና እንዲማሩ ማድረግ
- የተለያዩ የችሎታ መገምገሚያ ዘዴዎችን ይጠቀሙ ለምሳሌ፡- የቃል፣ የተግባር ሥራ፣ የጽሑፍ ወ.ዘ.ተ
- ተግባራትን እንዲያጠናቅቁ ተጨማሪ ሠዓት መስጠት
- እይታ የሚፈልጉ ይዘቶችን በሌላ ይዘቶች መቀየር (በሚነኩ በሚዳሰሱ ወ.ዘ.ተ)
- ግልጽ ባልሆኑ ይዘቶች ላይ ናሙና ወይም ትክክለኛ ቁስ በማቅረብ እየነኩ እንዲማሩ ማድረግ
- በቴፕ ድምጾችን ቀድተው ለጥናት አገልግሎቶች  እንዲጠቀሙበት ይፈቀድላቸው
- ክትትል እና ድጋፍ አይለያቸው

## 2.5.1.2 ከፊል የእይታ ተግዳሮት ላለባቸው ተማሪዎች ድጋፍ መስጠት

- ቤተሰብ ወጪን የመሸፈን አቅም ካላቸው ወደ ሐኪም ሄደው መነፅር ቢያገኙ የእይታ ችግራቸው ይታረማል፡፡
- በክፍል ውስጥ በተማሪዎቹ ምርጫ በሚታያቸው ቦታ እንዲቀመጡ መፍቀድ
- የእጅ ፅሑፍዎን መጠን ከፍ ማድረግ ሁሉም ተማሪዎች እንዲያዩት መድረግ
- ፈዛዘነት ወይም ደማቅነት ያላቸው ሁለት ቀለማትን በአንድ ላይ በጽሑፍ ጊዜ አለመጠቀም፤ለምሳሌ፡ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በአረንጓዴ ቾክ መጠቀም

- ክፍሉ ከፍተኛ የብርሃን መጠን ወይም ደብዛዛ ብርሃን እንዳይኖረው ማስተካከል
- መረጃዎች ጎላ ብለው እንዲታዩ ሆነው ማዘጋጀት
- ክትትል እና ድጋፍ ያድርጉ፤በአገልግሎት ማሻሻያ ላይ ከተማሪዎቹ ጋር ይወያዩ



## 2.6. የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ዳሰሳ

የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ደረጃ ፤ የፍላጎት ዓይነት እና መጠን ከአንድ ሰው ወደ ሌላው የሚለያይ ቢሆንም አብዛኞቹ ልጆች በመደበኛ ክፍል ውስጥ ገብተው ድጋፍ እየተደረገላቸው መማር የሚችሉ ናቸው፡፡ በተለይ ዝቅተኛ ደረጃ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት (mild) ያለባቸው ልጆች በአካላቸው ላይ ምንም ዓይነት መገለጫዎች ስለማይታዩባቸው የእነዚህን ተማሪዎች የትምህርት ፍላጎት ለይቶ ድጋፍ የመስጠት ልምዱ እና ክህሎቱ በትምህርት ቤቶች በጣም ውስን ነው፡፡ በዚህም ምክንያት የትምህርት ውጤታቸው ዝቅተኛ ነው፡፡ እነዚህ በዝቅተኛ ደረጃ የአእምሮ እድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች በአንድ ሀገር ውስጥ ይገኛሉ ተብለው ከሚገመቱት የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ካለባቸው ሰዎች ከ85% በላይ እንደሚሆኑ ይገመታል፡፡ ከዚህ አንፃር ዕድሜአቸው ለት/ት የደረሱ ዝቅተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ቁጥራቸው ከፍተኛ ከመሆኑም በላይ በመደበኛ ክፍል ውስጥ በመገኘታቸው ድጋፍ በማጣት አዘወትረው ክፍል ለመድገም እና ትምህርት ለማቋረጥ የተጋለጡ ናቸው፡፡

ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 7 የተዘረዘሩትን የአእምሮ ዕድገት ውስንነት መገለጫዎችን ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች ከየትኛው መገለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ባህሪ እንደሚያሳዩ ከለዩ በኃላ ተያይዞ የቀረበውን የድጋፍ ዝርዝር በመመልከት ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 7 የአእምሮ ዕድገት ውስንነት መገለጫዎች

| የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ዋና ዋና ክፍሎች | የአእምሮ ዕድገት ውስንነት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| ዝቅተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት (mild) | የተማሩትን ይዘት ወዲያው ወይም በሚቀጥለው ቀን አለማስታወስ | | |
| | ክፍል አዘውትረው መድገም | | |
| | ከክፍል ጓደኞቻቸው በተለየ የተማሩትንም ይሁን የተደረጉ ነገሮችን መርሳት | | |
| | ክፍል ውስጥ ብዙ ጊዜ ለጥያቄ የሚሰጡት መልስ የተሳሳተ መሆን | | |
| | በአብዛኛው የትምህርት ዓይነቶች ይዘቶችን አለመረዳት | | |
| | በትምህርት ጉዳዮች ላይ ብዙ ጊዜ በክፍል ጓደኞቻቸው ላይ ጥገኛ መሆን | | |
| | ትምህርት ነክ ባልሆኑ ተግባራት እንደጓደኞቻቸው በተመሳሳይ መተግበር | | |
| | በአብዛኞቹ ትምህርቶች ከአማካኝ ውጤት በታች ማስመዝገብ | | |
| | በትምህርታቸው ውጤት ዝቅተኝነት የተነሳ የባህሪ ችግር ማሳየት (ከተማሪዎች እና ከመምህራን ጋር መጋጨት) | | |
| | በትምህርታቸው ደካማ በመሆናቸው መምህራን እና ተማሪዎች ዝቅተኛ ግምት ስለሚሰጧቸው የተሻለ ግምት እንዲሰጣቸው ረባሾች መሆን፡፡ | | |
| ከፍተኛ ደረጃ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት | በሰውነት ዕድገታቸው ለንቋሳ መሆን | | |
| | ደካማ የእጅ እና የዓይን ቅንጅት | | |
| | ደካማ የሰውነት ቅንጅት (ሲራመዱ፤ ሲሮጡ…) | | |
| | የእጃቸው ጣቶች ጥንካሬ ማጣት | | |
| | ለክፍል ደረጃቸው የተዘጋጀን ይዘት አለመረዳት | | |
| | የንባብ እና ፅሑፍ ክህሎት ማጣት. | | |
| | በአካላቸው የቅንጅት ችግር ምክንያት ሲራመዱ ወይም ሲሮጡ አዘወትረው መውደቅ | | |
| | ዝቅተኛ የንግግር ቋንቋ ዕድገት | | |
| | ንግግራቸው ለአድማጭ ግልፅ ያለመሆን | | |
| | የሰለጠኑትን ወይም የተማሩትን መርሳት | | |
| | የዕለት ዕለት ክህሎት አለመዳበር ለምሳሌ፡- በዕድሜ የሚጠበቅ መፀዳጃ የመጠቀም ክህሎት፣ የመመገብ ክህሎት፣ የመልበስ ክህሎት፣ ንጽህና አጠባበቅ፣ የቤተሰባቸውን ማንነት እና ዝምድና አለመለየት | | |

### 2.6.1. ዝቅተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

- ተማሪዎችን ማበረታታት፣ በትምህርት ተስፋ መቁረጥን መቀነስ፣ ከትምህርት ጠቃሚነት ጋር ራዕይ እንዲኖራቸው መምከር ፤ትምህርት እንዳያቋርጡ ማገዝ
- በግል ወይም በትንሽ ቡድን ተጨማሪ የትምህርት ድጋፍ (tutorial) መስጠት
- አንድን ይዘት ደረጃ በደረጃ እንዲማሩት ማድረግ
- ውስብስብ ይዘቶችን በትንሽ በትንሹ እና ደረጃ በደረጃ በማስተማር እንዲረዱት ማድረግ
- አዳዲስ ይዘቶችን እና ሀሳቦችን ከተጨባጭ መረጃዎች ጋር በማጣመር ማስተማር
- የትምህርቱን ይዘት ከዕለት ተዕለት የህይወት ተሞክሮ ጋር ማስተሳሰር
- ማበረታታት (በቃል፣ ወይም በዓይነት)
- የተማሪዎቹን ትኩረት ለመሰብሰብ ሀሳብን በቀላሉ የሚበትኑ በክፍል ውስጥ ያሉ ነገሮችን ማስወገድ
- የተለያዩ የማስተማሪያ ዘዴዎችን እና ምሳሌዎችን መጠቀም
- ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት
- የተማሩትን በሙከራ እንዲሰሩ ዕድል መስጠት
- ቶሎ ስለሚረሱ በተደጋጋሚ መግለፅ
- ኢጋዥ እና እርማት የተጨመረበት አስተያየት መስጠት
- የተማሪዎቹን ችሎታ የተለያዩ መመዘኛዎች በመጠቀም ዳሰሳ ማድረግ
- የተማሪዎችን እገዛ ማመቻቸት
- ቤተሰብን በማነጋገር በቤት ውስጥ እገዛው እንዲቀጥል ማድረግ
- በየጊዜው ለውጥ ማምጣታቸውን ክትትል ማድረግ እና ድጋፍ መስጠት



**ተማሪዎች ዕድል ከተሰጣቸው ማንኛውንም ነገር መስራት ይችላሉ**

## 2.6.2. ከፍተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

ከፍተኛ የአእምሮ ዕድገት ውስንነት ያለባቸው ልጆች ተከታታይ እና ጥብቅ ድጋፍ ስለሚያስፈልጋቸው፤ መምህራንም ይህንን ፍላጎት በመለየት ጠቃሚ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡ የድጋፍ ዓይነት እና መጠን እንደ የአእምሮ ዕድገት ውስንነቱ ደረጃ ፤ እንደሚታዩ ፍላጎቶች ዓይነት እና መጠን ይለያያል፡፡አንዳንድ ልጆች የዕለት ተዕለት ህይወትን የመምራት ክህሎት፤ ማንበብ፤ መፃፍ እና ቁጥር ነክ የሆኑ ግንዛቤዎችን ውስን በሆነ መልኩ የመቀበል አቅም ሲኖራቸው፤ ሌሎች ልጆች ከትምህርት ይዘቶች በተጨማሪ መሰረታዊ ዕውቀት ሊያስጨብጡ የሚችሉ ክህሎቶችን መማር ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል አንዳንድ ልጆች የአእምሮ ዕድገት ውስንነቱ በጣም ከፍተኛ ከሆነባቸው በየዕለቱ ሊተገበሩ የሚገቡ ክህሎቶችን ብቻ መጨበጥ ይችላሉ፤ ስለዚህ በዚህ ደረጃ የሚገኙ ልጆች የፍላጎታቸው ዓይነት እና መጠን ስለሚለያይ ለእያንዳንዱ ልጅ በግብ የተተለመ ተግባር መተግበር ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ የተዘረዘሩት የድጋፍ ዓይነቶች ጠቃሚ ከመሆናቸውም በላይ እነዚህ ልጆች በተደጋጋሚ ከሰለጠኑ ክህሎቱን መጨበጥ እንደሚችሉ አስተማማኝ ነው፡፡

ሀ. የዕለት ተዕለት ተግባር ክህሎት ስልጠና

- ልብሳቸውን እራሳቸው እንዲለብሱ ማሰልጠን
- በተገቢው እራሳቸውን ችለው የቀረበላቸውን ምግብ እንዲመገቡ ማሰልጠን
- የመፅዳጃ አጠቃቀም እና ተያያዥ የንፅህና አጠባበቅ፤ እጅን መታጠብ ማሰልጠን
- እጃቸውን እና ፊታቸውን መታጠብን ማሰልጠን
- ተማሪዎች ቀላል የሰውነት እንቅስቃሴ እንዲያደርጉ ማለማመድ/ የጤና ችግር እስከሌለባቸው ድረስ፡፡
- ዓይን እና እጅን አቀናጅቶ መስራት ላይ ስልጠና መስጠት
- መላ ሰውነትን እና እጅን አቀናጅቶ መራመድን ማለማመድ (ተማሪዎቹ የመተንፈሻ አካል ወይም የልብ ችግር እንደሌለባቸው ከሐኪም ማረጋገጫ ቢያመጡ ይመረጣል፡፡ የአካል እንቅስቃሴው መጠን እና ዓይነት ሐኪም በሚያዘው መሰረት ይሁን፡፡
- ጓደኛ ማፍራት እና መጫወት የመሳሰሉትን ማህበራዊ ክህሎቶች ማሰልጠን
- በክህሎቶች መሻሻል ላይ ድጋፍ እና ክትትል አይለያቸው

ለ. ትምህርት

- ተማሪዎች ትምህርት መሳሪያዎቻቸውን በአግባቡ ለመያዝ እና ለመጠቀም ተደጋጋሚ ስልጠና ይሰጣቸው፡፡
- የእርሳስ አያያዝን በተደጋጋሚ ማሳየት እና ማለማመድ
- በውስን ደረጃም ቢሆን ፊደላትን እና ቁጥሮችን እንዲለዩ ተደጋጋሚ ድጋፍ መስጠት መጀመሪያ ያሳዩዋቸውን ሳይችሉ አዲስ ይዘት አለማስጀመር
- የሚማሩት ይዘት እንዲገባቸው በተጨባጭ እና ከአካባቢ በሚገኙ ናሙናዎች ደጋግመው ያስተምሯቸው
- እነዚህ ልጆች የመደበኛ ሥርዓተ ትምህርት ይዘቶችን በአብዛኛው መማር ስለማይችሉ የእነርሱን ችሎታ መሰረት ባደረገ መልኩ የሚመጥናቸውን ማስተማር ተገቢ ነው፡፡
- መጨበጥ የሚገባቸውን ክህሎቶች በመለየት ለእያንዳንዳቸው የዓመት ግብ መተለም በጣም ከመጥቀሙም በላይ ለክትትል እና ድጋፍ አቅጣጫ ይሰጣል፡፡

## 2.7. በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት ዳሰሳ

በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት ከልጆች ወደ ልጆች በዓይነቱ እና በመጠኑ ይለያያል፡፡ ይህ ክፍል የሚያተኩረው የአፍ መፍቻ ቋንቋቸውን በተገቢው ማሳደግ ስለሚቸገሩ ተማሪዎች ነው፡፡ በሰንጠረዥ 8 የተካተቱት በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት መገለጫዎች ናቸው፡፡ መምህር የተዘረዘሩትን በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት መገለጫዎች ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች ከየትኛው መገለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ባህሪ እንደሚያሳዩ ከለዩ በኋላ ተያይዞ የቀረበውን የድጋፍ ዝርዝር በመመልከት ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

**ተማሪዎች የመምህራን ነፀብራቅ ናቸው**

ሰንጠረዥ 8 የመግባባት ተግዳሮት መግለጫዎች

| ዋና ዋና ክፍሎች | የመግባባት ተግዳሮት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| የንግግር ድምፅ | አንዳንድ የንግግር ድምፆችን በተቀራራቢ ድምፆች መተካት (ለምሳሌ ተ- ረ) | | |
| | አንዳንድ የንግግር ድምፆችን በሚጠበቀው የድምፅ ጥራት አለማውጣት (ለምሳሌ "ከ" ን "ኸ" ብሎ መጥራት) | | |
| | በንግግር ውስጥ አላስፈላጊ እና ያልተለመዱ ድምፆችን ማስገባት | | |
| | አንዳንድ ድምፆችን ጨርሶ በንግግር ውስጥ አለማስገባት ለምሳሌ (መስመር- ለማለት መመር- ማለት) | | |
| የንግግር ፍሰት ችግር | ንግግርን መንተት፣ወይም ባልተፈለገ ፍጥነት መናገር | | |
| | መናገር ሲጠበቁ ከቁጥጥራቸው ወጪ በሆነ መንገድ ዝም ማለት | | |
| | ድምፆችን ወይም ቃሎችን መደጋገም | | |
| | መናገር ለመጀመር ፈራተባ ማለት | | |
| | የሚናገሩት ነገር ለአዳማጩ ግልፅ አለመሆን | | |
| | በንግግር መካከል እ..እ..እ..እ..ም የመሳሰሉ ድምፆችን አዘወትረው መጨመር | | |
| | በሰዎች ፊት መናገር መፍራት | | |
| | በሰው ፊት ንግግር ለመጀመር መቸገር | | |
| | ንግግር ለመጀመር ትግል እና መተንፈስ እስከሚቸግራቸው ለመናገር መታገል | | |
| ያተለመደ ድምፅ መጠን እና ቃና | የድምፅ መጠን በንግግር ጊዜ በጣም ከፍተኛ ወይም በጣም ዝቀተኛ መሆን | | |
| | የድምፁ ዓይነት ከተናጋሪው ዕድሜ፣ ፆታ እና ከአካባቢው ተናጋሪዎች ጋር ሲነፃፀር የተለየ መሆን (በቅላፄ፣በጎርናናነት፤ በቅጥነት....) | | |
| ንግግርን የመረዳት ተግዳሮት | ተማሪዎች የመስማት ችግር ሳይኖርባቸው ነገር ግን የንግግር ቋንቋን መልዕክት የመረዳት ተግዳሮት ማሳየት | | |
| Expressive language difficulty | ቋንቋን ይሰማሉ፤ ይረዳሉ፤ መልዕክት ሲሰሙ ይተባበራሉ፤ ነገር ግን አይናገሩም | | |
| | ሐሳባቸውን ለመግለፅ ምልክቶችን ወይም በጣት መጠቆምን፤ በፊት ገፅታ ማመልከትን ይጠቀማሉ | | |

### 2.7.1. በቋንቋ የመግባባት ተግዳሮት ላለባቸው ድጋፍ መስጠት

- በትምህርት ቤት የግንዛቤ ማሳደጊያ መስራት እና ከመግባባት መገለልን መቀነስ
- በቃል መናገርን ማበረታታት እና ሲሞክሩ መሸለም፤ ማበረታታት
- ተማሪዎችም ይሁኑ መምህራን እነዚህን ተማሪዎች እንይሰድቡ፣ቅፅል ስም እንዲያወጡላቸው ክትትል ማድረግ፡፡
- እንዳያላግጡባቸው መከላከል ምክንያቱም በቋንቋቸው የመናገር ተሳትፎአቸውን ይቀንሳል፡፡
- በየጊዜው ለውጥ መምጣቱን መከታተል እና መደገፍ

ሀ. የንግግር ድምፅ አወጣጥ ድጋፍ

- ተማሪዎች የንግግር ድምፅ ማውጣት ችግር በሌሎችም ልጆች ላይ እንደሚታይ እና እነሱ ብቻ እንዳልሆኑ አውቀው በራስ መተማመን እንዲያዳብሩ መምከር
- ተማሪዎች እንዳያላግጡባቸው ወይም በንግግራቸው ሁኔታ መገለል እንዳይደርስባቸው መከላከል
- ተማሪዎች በትክክል መጥራት የሚያቅታቸውን የድምፅ አይነቶች መለየት
- በአንድ ለአንድ ድጋፍ ድምፆቹን በትክክል እንዲሞክሩ ማለማመድ
- ከወላጆች ጋር በመነጋገር ተማሪዎቹ በትምህርት ቤት የሚደረግላቸውን ድጋፍ በቤት ውስጥም እንዲደረግላቸው ማወያየት
- ተማሪዎቹ በክፍል ውስጥ እንዲሳተፉ ዕድል መስጠት እና ማበረታታት
- ክትትል በማድረግ አንድን ድምፅ በትክክል ሲጠሩ ወደ ሌላው ድምፅ ማለማመድ መሸጋገር

ለ. የንግግር ፍሰት ተግዳሮት ማሻሻያ ድጋፍ

የንግግር ፍሰት ችግር ያለባቸው ልጆች በአዳማጮች መገለል ወይም ማሾፍ ሲደርስባቸው ንግግሩ የበለጠ ያስቸግራቸዋል፡፡ ስለዚህ የዚህ ዓይነቱን ማግለል ማስወገድ ይገባናል፡፡  መምህራን የተማሪዎችን ግንዛቤ በማሳደግ ተገቢ ያልሆነ አስተያየት ከመስጠት እንዲቆጠቡ እና ጓደኞቻቸው በመሆን የንግግር ፍሰት ችግር ያለባቸውን ልጆች አብረው በማጫወት ንግግራቸው እንዲሻሻል ድጋፍ እንዲሰጡ ማድረግ መሰረታዊ እና ጠቃሚ ድጋፍ ነው፡፡

- እነዚህ ልጆች በአእምሮ ዕድገታቸው ላይ ምንም ችግር የሌለባቸው በመሆኑ እና መደበኛውን ሥርአተ ትምህርት መማር ስለሚችሉ በትክክል አለመናገራቸው እንደ ትምህርት አለመቻል መገለጫ መቁጠር የተሳሳተ መሆኑን ግንዛቤ ማሳደግ
- ተማሪዎቹ የተናገሩት እንዳልገባዎት በማማረር ከመግለፅ የተማሪዎቹን ሐሳብ ለመረዳት የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም

- እነዚህ ተማሪዎች ለመናገር ሲሞክሩ የጉሮሮ እና የደረት ጡንቻቸው ስለሚወጣጠር በግል ደረጃ ጡንቻቸውን ፈታ አድርጎ መናገር ማለማመድ
- ትንፋሻቸውን በንግግር ጊዜ ፈታ ባለመንገድ እንዲተነፍሱ እና እንዳይጨናነቁ ዘና ማለትን ማለማመድ
- አፋቸውን፣ ጉሮሯአቸውን፣ አገጫቸውን፣ ዘና ባለ መልክ እንዲያንቀሳቅሱ ማለማመድ (ለምሳሌ፡- ማስቲካ የሚያኝኩ አስመስለው አፋቸውን ዘና ባለ መልክ ማንቀሳቀስ)
- ፈታ ባለመልክ ቃልን ማውጣት ማለማመድ፤ ሲያሻሽሉ የሚለማመዱትን ቃላት መጠን መጨመር፤በመጨረሻም ሙሉ ንግግር ማውጣትን ማለማመድ
- አንዳንድ ልጆች በሌላ በኩል የንግግር ደጋፊ ጡንቻዎቻቸው በጣም ልል በመሆናቸው በጣም በፍጥነት ብዙ ቃላት ስለሚያመጡ ንግግራቸው ለአድማጭ ለመረዳት ያስቸግራል፡፡ ስለዚህ የጡንቻ እንቅስቃሴዎቻቸውን በመቆጣጠር ፍጥነትን ቀንሰው ቃል እንዲያወጡ ማለማመድ፤ ቀስ ብለው አንድ ቃል በትክክል እንዲያወጡ ማድረግ፤ ሲችሉ የቃላት መጠን ደረጃ በደረጃ በመጨመር የጡንቻ እንቅስቃሴ እና የንግግር ፍጥነታቸውን እንዲቆጣጠሩ ማለማመድ
- ተማሪዎች አንዱን ክህሎት ሲጨብጡ ወደ ቀጣዩ ክህሎት እገዛ መሸጋገር

ሐ. ያልተለመደ ድምፅ ማሻሻያ ድጋፍ

- አንዳንድ ልጆች የላይኛው ላንቃ ወይም ከንፈራቸው ተከፍቶ ይወለዳሉ፡፡ በዚህ ጊዜ ንግግር ማድረግ ሲሞክሩ ድምፃቸው ወደ አፋቸው ጫፍ ከመድረሱ በፊት በአፍንጫቸው ይወጣና ንግግራቸው በአፍንጫቸው ይሆናል፡፡ እነዚህ ልጆች በቅድሚ ወላጆችን በማማከር ወደ ሐኪም ሄደው ሕክምና እንዲደረግላቸው ማድረግ ለምሳሌ፡- (በአዲስ አበባ የየካቲት 12 ሆስፒታል ይህን አገልግሎት ይሰጣል)
- ተማሪዎቹ የህክምና ድጋፍ ከአገኙ በኋላ የንግግር ድምፅ ወደ አፍ በማውጣት እንዲለማመዱ ማድረግ፤ የድምፅ አወጣጣቸውን ሲያለማምዱ በፆታቸው ዓይነት መሠረት በማድረግ ነው ለወንድ ወፈር ያለ ድምፅ ለሴት ቀጠን ያለ ድምፅን ማውጣት ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡
- የድምፅ ቅላፄያቸው ከፆታቸው ተቃራኒ ሲሆን በፆታቸው መሠረት ለወንድ ወፈር ያለ ድምፅ ለሴት ቀጠን ያለ ድምፅን ማውጣትን ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡
- በት/ት ቤት የሚደረግ ድጋፍ ቀጣይነት እንዲኖረው የቤት ውስጥ እገዛ እንዲኖር ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት መፍጠር፡፡
- ድጋፍ እና ክትትል ፤ የጓደኞቻቸውን እገዛ ማመቻቸት

መ. ንግግርን የመረዳት ክህሎት ማሻሻያ ድጋፍ

የንግግር ቋንቋን መረዳት የሚቸገሩ ልጆች በመምህራንና ወላጆች እንደመስማት የተሳናቸው ተማሪዎች ይቆጠራሉ፡፡ እነዚህ ልጆች መስማት የተሳናቸው አይደሉም፡፡

- እነዚህ ልጆች የንግግር ቋንቋን መረዳት እንዲችሉ ተጨማሪ የመግባቢያ ዘዴ እና ደጋፊ ቁሳቁስ መጠቀም ይገባል፡፡ ለምሳሌ፡- እውነተኛ ቁሳቁሶች እና ስሞቻቸው፤ ሥዕሎችና መግለጫዎች፣ የተፃፉ ቃላቶች፣ ፅሑፉን እየገለፁ የፅሁፉን መልዕክት በመተግበር በማሳየት የንግግር ቋንቋው የያዘውን መልዕክት እንዲረዱ ማድረግ
- ሐሳቦችን በቀላል አገላለፅ እና በውስን ቃላት ማስተማር
- አንድን ሐሳብ ከተረዱ በኋላ ለዛ ሐሳብ የተጠቀምንባቸውን ቃላት እንዲጠሩ ማለማመድ፡፡ እነዚህ ልጆች አንዳንዶቹ የመናገር ችሎታ እንዳላቸው የሚታወቀው የሰሙትን ነገር ሳይረዱት መልሰው ይሉታል ስለዚህ ድጋፉ ሐሳብን ከመረዳት ጋር ከሆነ የበለጠ ይጠቅማቸዋል፡፡
- እነዚህ ልጆች መስማት እየቻሉ ንግግርን መረዳት እና ቋንቋንም ማውጣት ስለሚቸግራቸው አማራጭ እና ተጨማሪ የመግባቢያ ዘዴን መጠቀም ያስፈልጋል ለምሳሌ የምልክት ቋንቋ
- በት/ት ቤት የሚደረግ ድጋፍ ቀጣይነት እንዲኖረው የቤት ውስጥ እገዛ እንዲኖር ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት መፍጠር፡፡
- ድጋፍ እና ክትትል በማድረግ ለውጦችን ያሳድጉ

ሠ. የንግግር ቋንቋን የማውጣት ድጋፍ

እነዚህ ልጆች ጥቂት የንግግር ቋንቋን ያወጣሉ ወይም ምንም ላያወጡ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን የሰሙትን የመረዳት ችግር የለባቸውም፤ የመስማትም ችግር አይታይባቸውም፤ነገር ግን ስለማይናገሩ ብዙ ጊዜ በትምህርት ቤት ውስጥ እንደመስማት የተሳናቸው ይቆጥሯቸዋል፡፡

- ድምፅ እንዲያወጡ ለማለማመድ መጀመሪያ ሌሎች ሲናገሩ ጉሮሮ ላይ የሚፈጠረውን መርገብገብ የመዳፋቸውን የውጪ አካል ተናጋሪው ጉሮሮ ስር በማድረግ እርግብግቢታን እንዲረዱ ማገዝ ፤ ከዚያም የመርገብገብ ስሜት እስኪሰማቸው በራሳቸው መለማመድ
- የንግግር ማውጣት ልምምድ አንድ ለአንድ በሆነ ድጋፍ ማድረግ
- ፈቃደኛ ተማሪዎችንም እንዲያለማምዷቸው ማጣመር
- እነዚህ ተማሪዎች የመደበኛውን ክፍል ሥርአተ ትምህርት መማር ይችላሉ፤ ሐሳባቸውን በቃል መግለፅ ባይችሉም በፅሑፍ መግለፅ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ መምህራን የትምህርት ይዘትን ግንዛቤ ዳሰሳ ሲያካሄዱ ከንግግር ውጪ ሌሎች አማራጮችን መጠቀም መልካም ነው፡፡ ምሳሌ፡- (በመፃፍ፣ ሰርቶ በማሳየት፤ በስዕል በመግለፅ ወዘተ)
- በትምህርት ቤት የሚደረግ ድጋፍ ቀጣይነት እንዲኖረው የቤት ውስጥ እገዛ እንዲኖር ከቤተሰብ ጋር ግንኙነት መፍጠር፡፡
- የንግግር ስልጠናውን ቀጣይ በማድረግ ድጋፍ መስጠት

## 2.8. የባህሪ ተግዳሮት ዳሰሳ

የባህሪ ተግዳሮት የተለያዩ መገለጫዎች አሉት ነገር ግን ለመምህራን የመለየት እና ድጋፍ የመስጠት ስራ እንዲረዳቸው ይህ ክፍል በሁለት ዋና ዋና የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች ላይ ያተኩራል፡፡ የሚከተሉትን መገለጫዎች በሰንጠረዥ 9 ይመልከቱ፡፡ መምህር፤ የተዘረዘሩትን የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች ከየትኛው መገለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ባህሪያት እንደሚያሳዩ ከለዩ በኃላ ተያይዞ የቀረበውን የድጋፍ ዝርዝር በመመልከት ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

**መምህር እባክዎ ተማሪዎች ትምህርት እንዳያቋርጡ የበኩልዎን ይርዱቸው**

ሰንጠረዥ 9 የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች

| ዋና ዋና ክፍሎች | የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| በውጫዊ መገለጫዎች የሚታዩ ባህሪያት | በትንሽ/ቀላል ነገር ግንፍልተኝነት | | |
| | የትምህርት ቤት ንብረቶችን ማውደም | | |
| | ከተማሪዎች እና ከመምህራን ጋር መጋጨት | | |
| | በቀላሉ መናደድ ፤ መቆጣት | | |
| | የሌሎችን ትኩረት መሳብ በመረበሽ፣ በመማታት፤የሌሎችን የመማሪያ መሳሪያ በማውደም ወ.ዘ.ተ | | |
| | የበላይነት ስሜት ማሳየት | | |
| | ሌሎችን በመጉዳት፣ በማስቀየም፣ በመረበሽ መማር ማስተማሩን ማስተጓጐል | | |
| | ቅብጥብጥ መሆን (በክፍል ውስጥ ቦታ መልቀቅ፣ መሮጥ፣ መዝለል) | | |
| | ዝቅተኛ ትምህርትን የመከታተል ትኩረት፤ ለረጅም ሰዓት አተኩረው አለማዳመጥ፤ ትኩረትን የሚፈልጉ ስራዎችን አለመስራት ወይም ጀምሮ መተው | | |
| | ስሜታቸውን አውጥተው በሚታይ መልኩ አካባቢን መረበሽ | | |

| ዋና ዋና ክፍሎች | የባህሪ ተግዳሮት መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|---|
| በውስጣዊ መገለጫዎች የሚታዩ ባህሪያ | ጭንቀት፣ ድብርት | | |
| | ብቸኛነት፣ ከማህበራዊ መግባባት መራቅ | | |
| | የበታችነት ስሜት | | |
| | በትንሽ ነገር መከፋት | | |
| | ስሜታቸውን ወደ ውስጥ አምቆ መያዝ | | |
| | የበዛ ዓይናፋርነት | | |
| | ብዙ ጊዜ ጥፍራቸውን መብላት፤ እርሳስ ወይም ልብሳቻቸውን ወደ አፋቸው አድርጎ መብላት | | |

## 2.8.1. የባህሪ ተግዳሮትን ለማሻሻል ድጋፍ መስጠት

ሀ. በውጫዊ መገለጫዎች የሚታዩ ባህሪያትን ለማሻሻል ድጋፍ

- የክፍል ውስጥ ሕጎች ማውጣት፣ ማሳወቅ፣ እንዲተገብሩ መከታተል
- የማይደገፉ ባህሪያትን ያለመሰልቸት ማረም ወይም አካላዊ ቅጣት ያልሆነ መገሰጫ መንገድ መጠቀም
- ተማሪዎቹን በመቅረብ በየጊዜው ማግኘት፣ ኃላፊነት መስጠት
- የተማሪዎችን የቤተሰብ ታሪክ በማጥናት ከባህሪዎች ጋር ግንኙነት ካለው መመርመር
- ወላጆችን በማነጋገር መነሻ የሆኑ የቤት ውስጥ ችግሮችን እንዲሻሻሉ ማድረግ
- ኃላፊነት በመስጠት በስራ እንዲያዙ ማድረግ
- ትምህርታቸው ላይ እንዲያተኩሩ በየጊዜው ምክር መስጠት
- በባህሪ ምክንያት የትምህርት ውጤታቸው ከቀነሰ ድጋፍ ማድረግ
- ለውጦች ሲታዩ መሸለም፤ማበረታታት
- የህይወት ህልም እንዲኖራቸው ማወያየት እና ህልማቸውን ለማሳካት የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መተንተን
- የባህሪ ለውጥ መምጣቱን በየጊዜው መከታተል

ለ. በውስጥ የሚገለፅ የባህሪ ተግዳሮት ድጋፍ

እነዚህ ተማሪዎች እንደዚህ ዓይነት ባህሪ ብዙ ጊዜ የሚያሳዩት ከኋላ/ከቤተሰብ ታሪካቸው ጋር የተያያዘ ነገር ሲኖር ስለሆነ ፤የቤተሰብ ታሪካቸውን ማጥናት ያስፈልጋል፡፡

- ስለዚህ ተማሪዎችን በማቅረብ ያለፈ ወይም አሁን ያሉበትን የኑሮ ሁኔታ ማጣራት
- መነሻው ከታወቀ ለማስወገድ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ
- ተማሪዎች ያጋጠማቸውን የህይወት ፈተና ወደኋላ በመተው የወደፊት ህይወታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ምክር መስጠት

- ጭንቀትን ለመቀነስ ከሌሎች መምህራን ጋራ በመነጋገር መፍትሔ ማዘጋጀት
- ከቤተሰብ ጋር ግንኑነት በመፍጠር የችግሩን መንስኤ ማስወገድ
- ማህበራዊ ግንኙነት እንዲያሻሽሉ ከተማሪዎች ጋር ማጣመር
- ጥሩ ማህበራዊ መግባባት ሲያሳዩ አበረታች ሽልማት ያደርጉላቸው
- ባህሪው ቶሎ ላይለወጥ ስለሚችል በትዕግስት ረዘም ላለ ጊዜ ድጋፍም አይለያቸው

# የነገውን ትውልድ ለሀገር የሚያስረክቡ መምህራን ብቻ ናቸው

## 2.9. ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ዳሰሳ

ልዩ ተሰጥኦና ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤቶች ፍላጎታቸው ብዙም ካለመታወቁም በላይ ምንም ድጋፍ አይደረግላቸውም፤ይልቁንም አንዳንድ መምህራን ስለማይረዷቸው ትምህርታቸውን ሊጐዳ በሚችል መልኩ አለመግባባት ሊፈጠር ይችላል፡፡

**ማስታወሻ:**

በክፍል ውስጥ አንደኛ መውጣት ማለት ተማሪዎች ልዩ ችሎታ አላቸው ማለት ላይሆን ይችላል። ምክንያቱም የክፍል ደረጃ አንፃራዊ ስለሆነ ፡፡ እነዚህ ልጆች አንዳንዴ ከመምህራኖቻቸው የበለጠ ዕውቀት እንዳላቸው መምህራን አይቀበሉም/አይገነዘቡም፤ በመሆኑም በመምህራን በጎ እይታ ስር አይሆኑም፡፡ ባጠቃላይ ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸው ልጆች ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፤ ከዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 10 የተዘረዘሩትን የልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ መገለጫዎች ይመልከቱ፡፡

መምህር፤ የተዘረዘሩትን የልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ መግለጫዎች ካነበቡ በኋላ ተማሪዎች ከየትኛው መገለጫ ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ባህሪያት እንደሚያሳዩ ከለዩ በኃላ ተያይዞ የቀረበውን የድጋፍ ዝርዝር በመመልከት ድጋፍ ያድርጉላቸው፡፡

ሰንጠረዥ 10 ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ መገለጫዎች

| የልዩ ችሎት እና ተሰጥኦ መገለጫዎች | ታይቷል | አልታየም |
|---|---|---|
| በትምህርት ከክፍሉ ይዘት ቀድሞ/ልቆ መገኘት | | |
| ራሳቸውን ችለው ይማራሉ/ይሰራሉ የሌሎችን እርዳታ አይፈልጉም | | |
| ከዕድሜአቸው በላይ የሆነ ዕውቀት እና ትልም አላቸው | | |
| ነገሮችን ከተለያየ አቅጣጫ ይመለከታሉ | | |
| በርካታ ነገሮችን እና ቅደም ተከተሎችን የማስታወስ ችሎታ አላቸው | | |
| በፍጥነት መማር እና መረዳት ይችላሉ | | |
| ከፍተኛ የሆኑ ትምህርት ነክ ነገሮች ላይ የመሳተፍ ፍላጐት አላቸው | | |
| ፈታኝ የሆኑ ተግባራት ላይ መስራትን መውደድ | | |
| የሌሎችን ድጋፍ ሳይፈልጉ በራሳቸው ችሎታ እና ፍላጐት በሰሩት ስራ መርካት | | |
| በአጠቃላይ ትምህርቶች ወይም በአንድ የትምህርት ዓይነት (ለምሳሌ ሒሳብ) ብቻ ላይ ልዩ የሆነ ችሎታ | | |
| የፈጠራ ችሎታ ማሳየት | | |
| ከፍትኛ የሥዕል ችሎታ | | |
| የሙዚቃ ችሎታ (ማቀናጀት/መምራት፤ድምፅ) | | |
| የላቀ ስፖርት ነክ ክህሎቶች መታየት ወ.ዘ.ተ. | | |

## 2.9.1.ልዩ ተሰጥኦ እና ችሎታ ያላቸውን መርዳት

- አንዳንድ ልጆች በሁሉም የትምህርት ዓይነቶች ልዩ ችሎታ አላቸው ለምሳሌ:- በአንድ ዓመት ሁለት ክፍሎችን በራሳቸው ፍጥነት ያለድጋፍ ማጠናቀቅ ይችላሉ፡፡ ስለዚህ እንደችሎታቸው ክፍል ማዘለል ጠቃሚ ነው፡፡ ይህንንም የክፍል መምህሩን፣ የትምህርት ቤት አስተዳደር እንዲሁም ወላጆች ተወያይተው እንዲወስኑ ማድረግ፡፡
- ተማሪዎች በአንድ የትምህርት አይነት ብቻ ልዮ ችሎታ ካላቸው የክፍሉን ትምህርት ይዘት ማበልፀግ፣ በዛ ትምህርት ላይ ከሌላ ክፍል ወይም ከሌሎች መጽሐፎች አማቅቸውን የሚመጥን ይዘት በነፍስ ወከፍ ማቅረብ
- እነዚህ ተማሪዎች በአንድ ተግባር ላይ ለረጅም ጊዜ በትኩረት የመስራት አቅም ስላላቸው ከክፍል ደረጃው ይዘት በላይ የሆኑ ተግባራት ላይ ማሰራት
- በክፍል ውስጥ ዕውቀታቸውን እንዲያካፍሉ ዕድል መስጠት
- አማራጭ የማሳተፊያ ዘዴዎች በመፈለግ ተማሪዎች በትምህርት ቤቱ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ማድረግ
- የትምህርት እና የፈጠራ ክበብ በመመስረት ተማሪዎቹ ባላቸው ችሎታ እና ተሰጥኦ መሰረት ክበቡን በመሪነት እንዲይዙ ማድረግ

- ተማሪዎቹን ማበረታታት
- መምህራኖች ተማሪዎቹ በሚሰሩት የፕሮጀክት ወይም የፈጠራ ክበብ አባል በመሆን እንዲያበረታቱዋቸው ማድረግ
- ተማሪዎቹ ትምህርት ቤቱን ወክለው የትምህርት ውድድር እንዲሳተፉ ማድረግ
- የፈጠራ ስራ የታከለበት የግል ወይም የቡድን ስራ መስጠት

## መምህራን የህይወት አቅጣጫ መሪዎች ናቸው

### 2.10. የእንቅስቃሴ ተግዳሮት ላለባቸው አካባቢን ምቹ ማድረግ

- የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ በቀላሉ ቢለዩም ትምህርት ቤቶች ለእንቅስቃሴ ምቹ ሆነው አያገኙአቸውም፡፡ አንዳንድ ትምህርት ቤቶች አካባቢውን ምቹ በማድረግ ተማሪዎች ምቹ እንቅስቃሴ ማድረግ እንዲችሉ ያግዛሉ፡፡
- በተቃራኒው አንዳንድ ትምህርት ቤቶች የእኛ ትምህርት ቤት ለእንቅስቃሴ ምቹ አይደለም በማለት የእንቅስቃሴ እግር ያለባቸውን ተማሪዎች አይቀበሉም፡፡ በተጨማሪ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች ዝቅተኛ የትምህርት ችሎታ ያላቸው አድርገው ይገምቷቸዋል፡፡
- ትምህርት ቤቶችን ምቹ ማድረግ ለምሳሌ፡- በአንድ ትምህርት ቤት አራት ወለል ያለው ፎቅ ላይ ተማሪዎች እንዲማሩ የሚጠበቅ ከሆነ ከእያንዳንዱ ክፍል አንድ አንድ ክፍል ለይቶ በምድር ወለል ቢመደብ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ልጆች እንደክፍል ደረጃቸው በምድር ወለል ላይ መማር ይችላሉ ፡፡ ሰለዚህ ርዕሰ መምህራን እና መምህራን የትምህርት ቤታቸውን አካባቢ ምቹ በማድረግ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸውን ተማሪዎች የትምህርት እድል ማመቻቸት ይጠበቅባቸዋል፡፡
- በተጨማሪ የስፖርት መምህራን፣ የጫወታ ሜዳዎችን ምቹ በማድረግ የእንቅስቃሴ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከስፖርት እንቅስቃሴ እንዳይገለሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ የተለየዩ የስፖርት አይነቶችንም እንደተማሪዎች ችሎታ ምቹ አድርጎ ተማሪዎቹን ማሳተፍ ይገባል፡፡

- በትምህርት ቤት ግቢ ውስጥ መፀዳጃ ቤቶች፣ የመጠጥ ውሃ ቦታዎች፣ ቤተ መፅሐፍት፣ ሻይ ቤቶች ለሁሉም ተማሪዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፤ ወደእነዚህ አገልግሎቶች የሚወስዱ መንገዶች ለእንቅስቃሴ ምቹ መሆን አለባቸው፡፡

## 2.11. ተደራራቢ ችግር ያለባቸውን መለየት እና ማገዝ

ተደራራቢ ችግር ያለባቸው ተማሪዎች ከአንድ በላይ ፍላጎት ስለሚኖራቸው ከተደራራቢ ጉዳቶች አንዱ በከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለ ይሆናል፡፡ ስለዚህ መምህራን የተደራራቢ ችግሮቹን ዓይነት እና የትኛው ከፍተኛ ተፅዕኖ እንዳለው መለየት ይኖርባቸዋል፡፡

ለምሳሌ፡- ተማሪዎች ዓይነስውርነት እና ከፊል የመስማት ችግር ካለባቸው፤ ብሬልን ለማስተማር ቅድሚያ በመስጠት ቀሪ የመስማት አቅምን ተጠቅሞ ስለብሬልም ሆነ ሌሎች ግንዛቤዎችን መስጠት ያስፈልጋል፡፡ ብዙ አይነት ተደራራቢ ችግሮች ስላሉ በዚህ የዳሰሳ መሣሪያ ውስጥ የተካተቱን ፍላጎቶች እና የድጋፍ ዓይነቶችን በማየት ተደራራቢ ተግዳሮቶች ያለባቸው ተማሪዎች ከየትኛው ፍላጎት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ተግዳሮቶች እንደሚያሳዩ በመለየት በተቀመጡ የድጋፍ አቅጣጫዎች ተማሪዎቹን ማገዝ ያስፈልጋል፡፡ ቅድሚያ ትኩረት የሚሻውን የፍላጎት ዓይነት በመለየት ቅደሚያ ድጋፍ መስጠት ወይም ከሌሎቹ ድጋፎች ጋር አጣምሮ መስጠት ጠቃሚ ነው፡፤

# Reference

Alberta Education (2006). Effective Student Assessment and Evaluation in the Classroom. Edmonton, Alberta

Calman, J. L. and Tarr-Whelan, L. (2005). Early Childhood Education for All: A Wise Investment. Legal Momentum, New York, NY

Cariappa, M. & Dang, G. (2005) Meeting Early Challenges: Special Step for a Special Child. New Delhi: UBSPD CfBT, (2014).

Davies, A. (2002). The social component of language teacher education. In H. Trappes-Lomax, & G. Ferguson (Ed.), Language in Language teacher education (pp: 49-66). Amsterdam: John Benjamin's B.V.

Hooten, G. R.(2009). The effect of handwriting, spelling, and T-units on holistic scoring with implication for dysgraphia. ProQuest LLC. UAS.

Hurlock, E.B. (2006) .Child Development (6th Ed). New York: Tata McGraw-Hill com.

Ingleson, L. and Lambert, K. (2007). Supporting Early Childhood Teachers through the use of Professional Learning Communities. Linking People and Resources, Norfolk.

UNRWA (2013). Teacher's Toolkit for Identifying and responding to Student's Divers Need.

Center for the Enhancement of Learning & Teaching.

UNESCO, (2008). The Contribution of Early childhood education to a sustainable society. France, Paris

# የነፍስ ወከፍ ድጋፍ መስጫ ቅፅ (IEP).

የትምህርት ዘመን___________

የተማሪው መግለጫ

የተማሪው ስም:________________________

ፆታ________________ ዕድሜ:___________________

የክፍል______ የትምህርት ደረጃ________________________________

የጤና ታሪክ__________________________________________.__

ቀደም ሲል የተደረገ የልዩ ፍላጎት አገልግሎት__________________________

የተማሪው ልዩ ችሎታ__________________________________________.

የተማሪው ልዩ ፍላጎት________________________________________.

## ለልዩ ፍላጎቱ የሚደረግ ድጋፍ

በመደበኛ ክፍል ውስጥ_______________________________________

በድጋፍ መስጫ ክፍል ውስጥ___________________________________

የድጋፍ ዓይነት.____________________________________________

በጤና. ________________________________________________

በትምህርት._______________________________________________

በማህበራዊ ክህሎት____________________________________________

አስፈላጊ ግብአቶች:____________________________________________

ለድጋፉ ባለድርሻዎች__________________________________________

የባለድርሻዎች ተሳትፎ ዓይነት_____________________________________

የሚጠበቅ ግብ_______________________________________________

ውጤትን መመዘኛ ዘዴ_________________________________________



FORMIN.FINLAND.FI

MINISTRY FOR FOREIGN
AFFAIRS OF FINLAND